አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

በድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በአዲሱ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጃት ንጽጽራዊ ግምገማ

በ

ጀማል ደዋ

መስከረም 2016 ዓ/ም

አዲስ አበባ

# በአዲሱ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጃት ንጽጽራዊ ግምገማ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

በድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተማር የማስተርስ ዲግሪ የቀረበ ማሟያ ጥናት

በ

ጀማል ደዋ

የጥናቱ አማካሪ

ዶ/ር ግርማ ገብሬ

መስከረም 2016 ዓ/ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በአዲሱ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ንጽጽራዊ ግምገማ

በ

ጀማል ደዋ

የስነሰብ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነት እና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነ-ፅሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ.......................ፊርማ.............ቀን...../ /2016ዓ/ም

ፈታኝ.......................ፊርማ.............ቀን..../ /2016ዓ/ም

ፈታኝ.......................ፊርማ.............ቀን..../ /2016ዓ/ም

ማውጫ

ይዘት ገፅ

ምሰጋና.......................................................................................................................I

የሰንጠረዥ ማውጫ...........................................................................................................II

አጠቃሎ.....................................................................................................................II

ምዕራፍ አንድ፤መግቢያ....................................................................................................1

1.1 የጥናቱ ዳራ ..................................................................................................1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት..........................................................................................3

1.3 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት...........................................................................................4

1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ......................................................................................................5

1.5 የጥናቱ ወሰን............................................................................................................6

1.6 የጥናቱ ውስንነት......................................................................................................6

1.7 የጥናቱ ቁልፍ ቃላትና ሀረጋት ብያኔ..............................................................................6

ምዕራፍ ሁለት፤ክለሳ ድርሳናት.......................................................................................... 8

2.1 የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ምንነት .............................................................................8

2.2 የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አስፈላጊነት ........................................................................8

2.3 የጽሕፈት ክሂል ትምህርት አላማ...................................................................................9

2.4 የጽሕፈት ክሂል ይዘት ምንነት.....................................................................................9

2.5 የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች ምርጫ..................................................................................11

2.5.1 ተገቢነት..........................................................................................................11

2.5.2 አስፈላጊነት.......................................................................................................11

2.5.3 ዘላቂነት............................................................................................................11

2.5.4 አስደሳችነት.......................................................................................................11

2.5.5 ለመማር ያላቸው አመቺነት.....................................................................................12

2.6 በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት........................................................................................................ 13

2.6.1 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት...............................................................114

2.6.2 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት.............................................................14

2.6.3 ተከታታይነት................................................................................. 15

2.6.4 ተለጣጣቂነት........................................................................................... 16

2.7 የቀደምት ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝት.................................................................17

**ምዕራፍ ሶስት፤የአጠናን ዘዴ**.........................................................................................20

**3.1 የጥናቱ ንድፍ**...................................................................................................20

**3.2 የጥናቱ የመረጃ ምንጮች**.....................................................................................20

3.3 የናሙናአመራረጥ ዘዴ..................................................................................21

3.3.1 የክፍል ደረጃ፤መማሪያ መጻሕፍት ናሙና አመራረጥ ዘዴ.................................. 21

3.3.2 የመጻሕፍት አዘጋጆች ናሙና አመራረጥ ዘዴ................................................ 21

**3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች**...............................................................22

3.4.1 ሰነድ ፍተሻ...................................................................................22

3.4.2 ቃለ መጠይቅ...................................................................................22

**3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ**.............................................................................23

3.5.1 የሰነድ ፍተሻ አተናተን ዘዴ...........................................................................23

3.5.2 የቃለ መጠይቅ አተናተን ዘዴ.........................................................................23

**ምእራፍ አራት፤የመረጃ ትንተና እና የውጤት ማብራሪያ**.......................................................24

**4.1 የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አጠቃላይ ቅኝት**.........................................................24

4.1.1 በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን ተግባራት ብዛት......................... 25

4.1.2 በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ትንተና........................................................................................ 26

**4.2 የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ምርጫ**.........................................................27

**4.3 በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት**..........................................................................................32

4.3.1 የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከተከታታይነት አንፃር...................................... 32

4.3.2 የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከተለጣጣቂነት አንፃር...................................... 40

4.3.3 የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት አንፃር......................... 46

4.3.4 የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት አንፃር.......................... 49

4.4 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ........................................................................54

ምዕራፍ አምስት፤ማጠቃለያ ፣ መደምደሚያ እና የመፍትሔ ሀሳብ 58

5.1 ማጠቃለያ ..........................................................................................58

5.2 መደምደሚያ .......................................................................................60

5.3 የመፍትሔ ሀሳብ ..................................................................................60

ዋቢ መጻሕፍት ............................................................................................ 62

አባሪዎች .................................................................................................. 65

ማረጋገጫ

# ምስጋና

ከሁሉ በፊት አስጀምሮ ላስጨረስኝ አላህ ምስጋና ይገባው፡፡ በማስከተል ይህ ጥናት ከውጥኑ ጀምሮ በዚህ መልኩ ተቃንቶ እስኪ ቀርብ ድረስ የጥናቱ ርእስ በማስተካከል ከመነሻው ትክክለኛ አቅጣጫ እንዲይዝ በማድረግ የጥናቱን ረቂቅ ከመነሻ እስከ መድረሻ ያለመሰልቸት በጥልቀት በማንበብ በጥናቱ የተለያዩ እርከኖች ላይ እጅግ ጠቃሚና ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮችን ከመጠቆም ባለፈ እያንዳንዱ ቃል ሀረግና አረፍተ ነገር በጥንቃቄ በማየት ስዋስዋዊም ሆኑ ሌሎች የሆሄያት ግድፈቶች በማቃናትና በመጠቆም እንዲሁም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ እርማት ምክር የማሻሽያና አማራጭ ሀሳቦችን በመጠቆም ከፍተኛ ሙያዊ ድጋፍ ላደረጉልኝ እናታዊና አባታዊ የማማከር ብልሀታቸውና ምክራቸው እንዲሁም ያሳለፍኳቸው አድካሚ አሰልቺ የስራ ሂደት መለስ ብዬ በማሰብ በቁዘማ ጊዜን እንዳላባክን ትልቅ ብርታት እየሰጡኝ ስራውን በትጋት እንዲከናወን ላደረጉልኝ ለአማካሪዬ ለዶ/ር ግርማ ገብሬ ታላቅ ልባዊ ምስጋናዬን አቅርባለሁ፡፡

ለጥናት ማከናወኛ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ከፍ ያለ ማስጋና አቀርባለሁ፡፡ በመቀጠልም ከጎኔ ሳይለዩ በርታ ላሉኝ ቤተሰቦቼና ባለቤቴ ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡

በመጨረሻም የጥናቱን ረቂቅ በኮምፒተር በመፃፍ፣ ስህተቶችን ለቅሞ በማረምና በማስተካከል የረዳኝ ታላቅ ወንድሜ አስፋው ደዋ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

## የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 1. የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አጠቃላይ ቅኝት......................................25
ሰንጠረዥ 2. በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የተግባራት ብዛት...............25
ሰንጠረዥ 3. በቋንቋ መማሪያ ጻሕፍት ውስጥ በጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ላይ የቀረቡት ተግባራት ብዛ..........................................................................27
ሰንጠረዥ 4. በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ብዛትና መገኛ ገፅ ማብራሪያ..................................................................29
ሰንጠረዥ 5. በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መፃሕፍ ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከተከታታይነት አንፃር የቀረቡት ተግባራት ብዛት.......................................................33
ሰንጠረዥ 6. በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከተከታታይነት አንፃር የቀረቡት ተግባራት ብዛት......................................................38
ከሰንጠረዥ 7. የዘጠነኛ እና የአስረኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህር ትይዘቶች የስርጭት መጠን ከተለጣጣቂነት አንጻር፤.........................42
ክሂል ትሰንጠረዥ 8. በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የጽሕፈት ምህርት ይዘቶች ማብራሪያዎች ፣ ብዛት ፣ አይነትና መገኛ ገፅ.............................................52

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና በአዲሱ የ9ኛእና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጃት በንጽጽር መገምገም ነው። ጥናቱ ሶስት መሰረታዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ይህንን አላማ ለማሳካት የተመረጠው ገላጭ የምርምር ንድፍ ሲሆን የተገኙት መረጃዎች ተሰብስበው በመጠናዊና በአይነታዊ የምርምር ዘዴዎች ተተንትነዋል፡፡ ለዚህ ጥናት የተመረጡት የዘጠነኛ እና የአስረኛ (9ኛ-10ኛ) የክፍል ደረጃ መማሪያ መጻሕፍት በ2015ዓ.ም ለሙከራ ስራ ላይ የዋለትን መማሪያ መጻሕፍት በአላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ በእነዚህ ሁለት የክፍል ደረጃዎች ውስጥ መማሪያ መጻሕፍትን በማዘጋጀት ላይ ከሚገኙት ውስጥ አንድ የመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጅ ቃለ መጠይቅ ተደረገሏ፡፡ ጥናቱ ለማካሄድ በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት የተለያዩ ምዕራፍችና ገፆች ውስጥ የሚገኙትን የመፃፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶች በሰነድ ፍተሻ ተለይተው ተሰብስበዋል፡፡ ለጥናቱ የሚያስፈልጉት መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኃላ በይዘት አደረጃጀት መርሆች ትንትናና የአተናተን ዘዴ መሰረት በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ያሉትና የሌሉት ይዘቶቹ በአይነት ተለይተው ተተንትነዋል፡፡ በተገኘው ውጤት መሰረት በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ብዛት 21 ሲሆን አማካኝ የድግግሞሽ መጠናቸውም 87.5% ሆኖ ተከታታይነታቸውን ጠብቀውና ስፋት ጥልቀታቸውን እየጨመሩ የመሄድ ሁኔታ ታይቶባቸዋል፡፡ ነገር ግን በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ 29.8% የሚደርሱ የመፃፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶች አንዴ ብቻ ቀርበው ሳይደጋገሙ መኖራቸው ለማየት ተችሏል፡፡ ከተደራጁት 21 የየጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ውስጥ 9ኙ ብቻ ተለጣጣቂነት ሲቀርቡ የተቀሩት 12ዎቹ ደግሞ ተለጣጣቂነታቸው ሳይጠብቁ የቀረቡ መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል፡፡ በጥናቱ ውጤት መሰረትም በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚቀርቡ የመፃፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶች በሁለም የእርከኑ መጻሕፍት ውስጥ ተለጣጣቂነት/ ቀጣይነት/ እንዲኖራቸው ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እና እንደ አስፈሊጊቱ የተማሪዎች ዳራ መሰረት በማድረግ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስልት አደረጃጀት አመጣጥኖ ማቅረብ ወደ አንድ ስልት ብቻ አለማመዘን የሚሉት በመፍትሔነት ተጠቁሟል፡፡

# ምዕራፍ አንድ፤መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ ተማሪዎች እየተማሩት ባለው ቋንቋ እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግ ብቻ ሳይሆን አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ብቃት በማዳበር እንዲግባቡበት ማድረግ ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ የመማሪያ መሳሪያዎች ሚና ከፍተኛ ነው። ስለ ቋንቋ ትምህርት ሲነሳ ቁልፉን ቦታ የሚይዙት የመማሪያ መሳሪያውች መሆናቸውን በተለያዩ ጊዜያት በቋንቋ ትምህርት ዙሪያ ጥናታቸውን ያደረጉ ተመራማሪዎች Grant(1987)፤ Cunningsworth(1995) እና Richards (2001) ገልፀዋል።

የማስተማሪያ መስሪያዎች የምንላቸው ስርአተ ትምህርት፤መርሃ ትምህርት፤የተማሪው መማሪያ መፃሀፍና የመምህሩን መምሪያ ያጠቃልላል። እነዚህም መሳሪዎች የቋንቋን ትምህርት ሂደት የተሳካ እንዲሆን የሚያግዙ የትምህርት መሰሪያዎች ናቸው። የማስተማሪያ መሳሪያዎችን ዝግጅት በተመለከተ ምሁራን እንደሚከተለው አብራርተዋል።

*ተስፋዬ (1981) የቋንቋ ማስተማሪያ መሰሪያዎች የሚባሉት ሆን ተብለው ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተዘጋጁት ወይም የተመደቡት ብቻ ናቸው። ሆን ተብለው ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተዘጋጁት ለአንድ የተወሰነ ክፍል እንዲያገለግሉ ስርአት ትምህርቱን ወይም የክፍሉ ተማሪዎች ሊኖራቸው ይችላሉ ተብሎ የምንገምተውንነ ችሎታ መሰረት በማድረግ ለማስተማሪያ ተብለው የሚዘጋጁ ናቸው።*

በማለት ገልፀዋል። እንዲሁም Richard and Rodgors (1986) በበኩላቸው የቋንቋማስተማሪያ መጻሐፍት ቋንቋ መማር ማስተማር ሂደትን የሚመሩ፤ የቋንቋ ትምህርቱን መናሻና መድረሻ የሚጠቁሙ የተለያዩ ይዘቶችን በምሣሌ አስደግፈው የሚያቀርቡ፤ መልመጃዎችንና የተለያዩ ተግባራትን በማቅረብ ተማሪዎችን እንዲለማመዱ የሚያደርጉ አጠቃላይ የመማር ማስተማር ሂደት እንቅስቃሴ መረጃ የሚሰጡ በመሆናቸው በጥንቃቄ ሊዘጋጁ እንደሚገባቸው ገልፀዋል።

የቋንቋ መማሪያ መፃሐፍት ለቋንቋ ትምህርት ግብ መምታት ጠንካራ የሃይል ምንጭ ናቸው። በተለይም በተጠቃሚዎች፤ በአዘጋጆዎች፤በተማሪዎች፤በመምህራንና በማህበረሰቡ ዘንድ ከፖሎቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ከማህበራዊ ጠቀሜታ አንጻር ያላቸው ተፈላጊነት ከፍተኛ ነው።

Hutchlson and Torres (1994 ) የቋንቋ መማሪያ መጸሀፍት የሚዘጋጁት የቋንቋ መርሃ ትምህርትን መሠረት አድርገው ነው። የቋንቋ መማሪያ መጻሐፍት መርሃ ትምህርትን መሰረት በማድረግ የሚዘጋጁ የትምህርት መማሪያዎች ናቸው። ቋንቋን ለመጠቀምም የመነሻ ጹሁፍ ሆነው ያገለግላሉ (Harmer፤1992)። መርሃ ትምህርት ውስጥ ከሚዘረዘሩት ነገሮች መካከል አንዱ የቀረበው የቋንቋ ትምህርት ይዘት ነው። እነዚህ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችም በመማሪያ መጻሐፍት ውስጥ በእቅድ የሚሰፍሩ እና በስርዓት የሚደራጁ ናቸው። Cunningsworth (1995) የቋንቋ ትምህርት ይዘት ስናደራጅ የሚከተሉትን ነጥቦች ማገናዘብ አስፈላጊ ነው። በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተማሪው መጀመሪያ ሊማር የሚገባው መሰረታዊ ይዘት የትኛው ነው?፤ የትኛው የቋንቋን ይዘት ለመማር ቀላል ነው?፤ እያንዳንዱን የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ለማስተማር የሚያግዙ ሌሎች የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች አሉ ወይ? ወዘተ የሚሉትን ጥያቄዎች የሚመልስ መሆን ይኖርበታል ሲሉ ይገልጻሉ። Nunan(1988) የቋንቋ ትምህርት ይዘት በተማሪዎች የክፍል ደረጃ ላይ የተካተቱትን የዋና ዋና እና የንዑሳን ርዕስ ጉዳዮች ይዘቶች የሆኑትን ጉዳዮች የሚያመለክቱ ሲሆን ተማሪዎች እንዲማሩ የተፈለገውን የቋንቋ እውቀት የክሂሎች ግንዛቤ አመለካከትን የሚገልጽ በቋንቋ ተፈጥሮን በቋንቋ ክሂሎች ግንዛቤ አመለካከትን የሚገልጽ በቋንቋ ተፈጥሮና በቋንቋ መማር ንድፍ ሃሳብ ላይ የሚመሰረት ነው።

ከእነዚህ ሃሳቦች እንደምንረዳው አንድ የቋንቋ መማሪያ መጸሐፍት የሚቀርበው ወይም የሚዘጋጀው በመረሐ ትምህርት ይዘት አደረጃጀት ውስጥ ለተማሪዎች የሚዘጋጅላቸውን የክፍል ደረጃ እንዲማሩና በዚያው የክፍል ደረጃ ውስጥ የተፈለገውን የቋንቋ ዕውቀት፤ የቋንቋ ክሂሎች ወዘተ መለየታቸው የምናውቅበት ነው።

የቋንቋ መማሪያ መፃሐፍ የሚዘጋጀው በቋንቋ መርሃ ትምህርት መሰረት እንዲሆን በስፋት ተገልጾዋል። በመርሃ ትምህርት ውስጥ ከሚዘረዘሩት መካከል አንዱ ለትምህርት የሚቀርበው የቋንቋ ትምህርት ይዘት ነው። ይህም ከእያንዳንዱ የቋንቋ እውቀት ደረጃ ወደ ሚቀጥለው የእውቀት ደረጃ ሲሸጋገር የሚሰጠው ትምህርት የተመጣጠነና እድገቱን የጠበቀ መሆን እንዳለበት የሚያመልክት ነው። የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች ለጽሕፈት ክሂል አላማ የሚመረጡ የቋንቋ አካላት ናቸው። የጽሕፈትን ትምህርትና የክሂሉን ባህሪይም መሰረት በማድረግ በቋንቋ ስርዓትና አጠቃቀም ይገልጻሉ። የይዘቶቹ አደረጃጀት ደግሞ በመማሪያ መፃሐፍ ውስጥ እንዴት ባለ ቅደም ተከተል መቅረብ እንዳለበት፤ የትኛው ከትኛው መቅደም እንዳለበት፤ የትኛው ደግሞ መከተል እንዳለበት የሚያመለክት ሳይንስ ነው Tyler (1949)።

በተጨማሪም ይዘቶች እንዴት ባለ መንገድ ተደጋግመውና ጥልቀታቸው እየጨመረ መቅረብ እንዳለባቸው ያሳያል፡፡ ከዚህም በመነሳት አደራጃጀት ከቀላል ወደ ከባድ፤ ተጨባጭ ከሆነው ወደ ረቂቁ/የተገላቢ ጦሻቸውን /እንዲሁም ድግግሞሽን ይመለከታል ማለት ይቻላል (Cunningsworth 1989 እና Nunan 1988)፡፡

በመጽሐፍት ዝግጅት ወቅት ምን ይቅደም? ምን ይከተል? ምን ይሻሻል በምን በምን ይጠናቀቅ የሚሉ ጥያቄዎችን የመመለስ ውሳኔ የመጽሐፍቱና የመርሃ ትምህርቱ አዘጋጆችን የደረጃ፤ ተለጣጣቂነትና ውህደት ግንዛቤ እምነታቸውን ያንጸባርቃል፡፡ ሰይድ(1993)‹‹ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘትን ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ትግበራ ግምገማ፡፡›› በሚል ርዕስ በሰባት የአደስ አበባ ትምህርት ቤቶች ጥናታቸውን ያካሄዱ ሲሆን ተሸለ(2005) ‹‹የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክሂሎችን፤ ይዘቶችን፤ መልመጃዎችን፤ አቀራረበን አደረጃጀት፡፡›› በሚል ርዕስ አቅርቧል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም በ2015 ዓ.ም ለሙከራ ተግባር ላይ በሚውሉት በአዲሱ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሐፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችን ከይዘት አደረጃጀት መርሆች አንፃር በንጽጽር መገምገም ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚው ይህንን ጥናት ለማካሄድ ካነሳሱት ምክንያቶች መካከል የተለያዩ ምሁራን የቋንቋ መማሪያ መጽሕፍት በየጊዜው መገምገም እንዳለባቸው እና ከችግሮች እንዳልጸዱ የሚያቀርቡት ሀሳብ ተጠቃሽ ነው፡፡

Donough and show(1995) ግምገማ የሚያስፈልገው ስራ ላይ ያሉ መጻሕፍትን ጠንካራና ደካማ ጎኖቻቸውን ለመለየት ሲሆን አዲስ የሚዘጋጁትን መጻሕፍት ደግሞ ተገቢነታቸውን ለማረጋገጥ ነው ይላሉ፡፡ Grant(1988) ደግሞ የመማሪያ መጽሕፍት ትኩረት ሰጥቶ የመገምገምን ተገቢነት ሲያስረዱ ‹‹ምንም አይነት ችግር የሌለባቸው የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አዘጋጅቶ ማቅረብ አይቻልም›› ይላሉ፡፡ ከነዚህ ምሁራን ሀሳብ መረዳት እንደምንችለው መማሪያ መጻሕፍት በየጊዜው እየተገመገሙ መሻሻል እንዳለባቸው የሚጠቁም በመሆኑ ይህንን ጥናት ለማካሄድ አነሳሽ ምክንያት ሆኗል፡፡

ሌላው አጥኚው በተተኳሪዎቹ የክፍል ደረጃዎች በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ያገለገሉ ሲሆን በእነዚህ ጊዜያትም ሆነ ቀደም ሲል በአገልግሎት ላይ በነበሩት መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የነበሩ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት የሚመለከቱ የይዘቶች አደረጃጀት ጥያቄ ሲፈጥርበት ቆይቷል፡፡

በተጨማሪም በተለያዩ ጊዜያት የተሰሩ ጥናታዊ ፅሁፎች መካከል ይህንኑ ጉዳይ የሚያረጋግጡ ፅሁፎች መኖራቸውን ተመልክቷል፡፡ አያሌው አሰፋው(1986) የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በማጥናት፣ይዘቶቹ የብቃት ማነስና የአደረጃጀት ጉድለት እንደሚታይባቸው ያመለከቱ ሲሆን አንተነ አወቀም(1974) በበኩላቸው የስነ-ፅሑፍ ይዘት በሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የተሰጠውን ትኩረት በመመርመር ለስነ-ፅሑፍ ትምህርት አነስተኛ ትኩረት መሰጠቱን፣የይዘት አደረጃጀት ችግርና የብቃት ጉለቶች መኖሩን ገልጸዋል፡፡

ጌታቸው አዱኛም(1985) ለአስረኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ምንባቦችን የብቃት ደረጃ ለመለካት ባደረጉት ጥናት ምንባቦቹ ተነባቢነት የሌላቸውና ለተማሪዎች ፍላጎት ያላቸው ቀረቤታ መካከለኛ መሆኑን ያመላከቱ ሲሆን፤ በነዚህ ጥናቶች የጽሕፈት ክሂልን ይዘቶች አደረጃጀት አስመልክቶ የተነሳ ነገር የለም፡፡

በሌላ መልኩ ሰይድ(1993) ‹‹በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘትን ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ትግበራ ግምገማ፡፡›› በሚል ርዕስ በሰባት የአደስ አበባ ትምህርት ቤቶች ጥናታቸውን ያካሄዱ ሲሆን ተሾለ (2005) ‹‹የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክሂሎችን፤ይዘቶችን፤መልመጃዎችን፤ አቀራረበን አደረጃጀት፡፡›› በሚል ርዕስ አቅርቧል፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነተ ያላቸው ቢሆንም ይሄኛው ጥናት ግን ከቋንቋ ክሂሎች ውስንነት አንጻር ከአጠናን ዘዴ አንጻር ከተጠኘው መማሪያ መጽሕፍት አዲስነት አንጻር እና ከጥናቱ አላማ ወዘተ አንጻር ሰፊ ልዩነት አላቸው፡፡

በመሆኑም በተተኳሪዎቹ 9ኛእና 10ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት መርሆዎች አንጻር የተሰጣቸው ትኩረት ምን እንደሚመስል በጥናት ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑ ሌላው አነሳሽ ምክንያት ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአዲሶቹ በሙከራ ስራ ላይ በዋሉት በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት የይዘቶች አደረጃጀት ንጽጽራዊ ግምገማ ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡ በዚህ አብይ አላማ ስር ሊነሱ የሚችሉ የተለያዩ ንኡሳን አላማዎች አሉት፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የ9ኛእና የ10ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ምን ምን አይነት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች እንደተካተቱ መለየት፣

- በ9ኛና በ10ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችን አደረጃጀት ከአደረጃጀት መስፈርቶች ማለትም ከተከታታይነት፣ ከተለጣጣቂነት፣ ከቅለትና ክብደት ደረጃ አንፃር መደራጀታቸው በንፅፅር መገምገም፤
- የ9ኛእና10ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ምህርት ይዘቶችና የአደረጃጀታቸውን ምላተ ቀርነታቸውን በንፅፅር መፈተሽ ሲሆኑ፣
- ከውጤቱ በመነሳት አስታየት መሰንዘር ናቸው፤

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችን በዝግጅት ወቅት ሆነ ተዘጋጅተው በስራ ላይ ከዋሉ በኋላ በቀጠይነት መገምገመቸው ይዘቶቹ በሂደት ለማሻሻልና ጥንካሬያቸውንም እየጎላ እንዲሄድ ለማድረግ የሚያስችል አስተዋፅኦ አላቸው። ይህ ጥናት ይህንን ሁኔታ የሚመለከት እንደመሆኑ መጠን ጥናቱ ሲጠናቀቅ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል።

- በጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ረገድ በ9ኛና በ10ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ የታዩትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በማሳየት ጠንካራ ጎኑ ተጠናክሮ የሚቀጥልበትን፣ደካማ ጎኑ ደግሞ  የሚሻሻልበትን አቅጣጫ ለቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ አዘጋጆች ይጠቁማል።
- በዘጠነኛ እና በአስረኛ (በ9ኛእና በ10ኛ) ክፍል በአማርኛ የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችን አደረጃጀት በመፈተሽ ምን አይነት ገፅታ እንዳለው በመጠቆም በመስኩ ለሚደረግ ቀጣይ ጥናት የበኩሉን አስተዋጾ ያበረክታል።
- የደረጃውን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ለሚያዘጋጁና የሚያሻሽሉ አካላት በዝግጅታቸውም ሆነ በማሻሻል ሂደታቸው ሊገለገሉባቸው የሚችሉ ግብኣቶችን በአቅሙ ይጠቁማል።
- የቋንቋ መምህራን ይህን ጥናት የማየት እድል ቢገጥማቸው የሚያስተምሩባቸው መፃሕፍት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት የይዘታቸውን አደረጃጀታቸው ለመገምገም የሚያስችላቸውን መነሻ ሀሳብ ሊያገኙበት ይችላሉ።
- በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ሰፊ ጥናት ለሚያደርጉ አጥኚዎች /አካላት እንደ መነሻ ሀሳብበመሆን ፍንጭ ይሰጣል።

### 1.5 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የሚያተኩረው ለሙከራ ስራ ላይ በዋሉት አዲሶቹ የ9ኛእና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት የይዘቶች አደረጃጀት በመፈተሽ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በእነዚህ የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በርካታ በመሆናቸው የተነሳ የሁሉንም ይዘቶች አደረጃጀት መፈተሽ ሰፊ ጊዜ ስለሚጠይቅ ጥናቱ የሚያተኩረው ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ላይ ብቻ ይሆናል፡፡ ይህም አሁን ለሙከራ ስራ ላይ ያሉትን የዘጠነኛ እና የአስረኛ (9ኛእና 10ኛ) ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ብቻ የሚፈተሽ ይሆናል፡፡ ጥናቱ ከተተኳሪ እርከን በታች ሆነ በላይ ያሉትን የመማሪያ መጻሕፍትም ሆነ አስቀድሞ በስራ ላይ ውለው የነበሩትን የመማሪያ መጻሕፍት፣ ማስተማሪያ መጻህፍት የመምህሩ መምሪያ እና ከተተኳሪው የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ውጪ ያሉትን ሌሎች የክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ይህ ጥናት አይመለከትም (አያካትትም)፡፡

### 1.6 የጥናቱ ውስንነት

አጥኚው ይህን ጥናት ሲያከናውን በርካታ ችግሮች አጋጥሞታል፡፡ ካጋጠሙት ችግሮች መካከል በተተኳሪው ክፍል ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በቃለ መጠይቁ ለማሳተፍ መጽሕፍቶቹ ሙከራ ላይ ስለነበሩ ሙከራው በተመረጡ ትምህርት ቤቶች የተወሰነ መሆን በቃለ መጠይቁ ለማሳተፍ አለመቻል፤ሌላው ከ10ኛክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍት አዘጋጆች በአድራሻ ለውጥ በቦታ ርቀት ምክንያት በቃለ መጠይቁ ማሳተፍ አለመቻል አብዛኛው የተደረገው ሰነድ ፍተሻው በመሆኑ የጥናቱን ውጤት ውስን አድርጎታል፡፡

### *1.7 የጥናቱ ቁልፍ ቃላትና ሀረጋት ብያኔ*

በዚህ ጥናት ውስጥ በተደጋጋሚ በመቅረብ ሰፊ ሽፋን ያገኙ ቃላትና ሀረጋት በጥናቱ ውስጥ ያላቸው ፍቺዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ✓ ***የመማሪያ መጽሐፍ፡-****የመማሪያ መጽሃፍ የሚባለው የአንድ ትምህርት አይነት አጠቃላይ ይዘቶችን አካቶ የያዘ ጥራዝ ነው ፡፡*

- ✓ ***የመፃፍ ክሂል ይዘት*** ፡- የሚለው ሀረግ በጥናቱ ውስጥ የያዘው ፍቺ ለማስተማሪያነት በሚዘጋጁ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የመፃፍ ክሂል ይዘትን ለማለማመድ የሚቀርቡ ይዘቶች በተገቢው መንገድ መደራጀት አለመደራጀታቸው የምንለይበት ስሌት ነው፡፡

- ✓ **የይዘት አደረጃጀት**፡- ይህ ሀረግ በዚህ ጥናቱ ውስጥ የተለያዩ መስፈርቶች መሰረት አድርገው የተቀመጡ ይዘቶችን በወል የሚያያዙበትና የሚያደራጁበት ስልት ነው፡፡
- ✓ **የመፃፍ ክሂል** ፡- ከዘጠነኛ እስከ አስረኛ ክፍል በሚዘጋጁ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የመጻፍ ክሂል ተግባራትን አደረጃጀትን ለተለያዩ አላማዎች ለማዋል ለተደራሲያን የሚገለፅበት መንገድ ነው፡፡
- ✓ **ተከታታይነት**፡-ይህ ቃል በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የመፃፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት በተጠቀሰው የክፍል ደረጃ ውስጥ አለያም ከቀጣዮቹ የክፍል ደረጃዎች ጋር የተካተቱን ይዘቶች ላላቸውን እድገት እየሰፉና እየተደጋገሙ መምጣታቸውን የሚያመለክት ነው ፡፡
- ✓ **ተለጣጣቂነት**፡- በተተኳሪዎቹ የክፍል ደረጃዎች በሚዘጋጁ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የመጻፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት የሚመለከቱ ጉዳዩችን /ተግባራትን/ በየደረጃው ስፋታቸውና ጥልቀታቸው እያደጉ ወይም እየሰፉ በእያዳንዱ መማሪያ መጻሕፍት ልዩ ልዩ ምዕራፎች ውስጥም ሆነ በቀጣዮቹ የክፍል ደረጃዎች ይዘቶቹ በቀጣይነት መደራጀታቸውን የሚመለከት ነው

# ምዕራፍ ሁለት፤ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ምንነት

የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት መርሃ ትምህርቱ ውስጥ የተቀረጸውን የትምህርት ይዘቶች ተማሪው ሊተገብራቸው በሚችልበት መልኩ የቋንቋውን አብይና ንዑሳን ክሂሎች ለማስተማር የተዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ Richard (2001) እንደሚገልጹት የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ማለት ተማሪው አስፈላጊውንና የታለመውን የቋንቋ ግብዓት እንዲለማመድ ለማስቻል ዕድሉን የሚፈጥሩ ዋነኛው የትምህርት መሳሪያዎች እንደሆኑና በቋንቋ ትምህርት መርሃ ግብር ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን ያብራራሉ፡፡ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ተቀዳሚ ተግባሩ የተማሪዎችን የስነ ልሳንና የቋንቋ ተግባቦታዊ ብቃትን ለማዳበር ይረዳ ዘንድ ለማስተማሪያነት የሚዘጋጅ ጽሁፍ ነው በማለት Sheldon ed (1987) ይገልጻሉ፡፡

## 2.2 የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አስፈላጊነት

የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ለቋንቋ ትምህርት ግብ መምታት ጠንካራ የኃይል ምንጮች ናቸው፡፡ በተለይም በተጠቃሚዎች፣ በአዘጋጆች፣ በተማሪዎች፣ በመምህራንና በማህረሰቡ ዘንድ ከፖሎቲካዊ፣ ከኢኮኖሚያዊና ከማህበራዊ ጠቀሜታ አንጻር ያላቸው ተፈላጊነት ከፍተኛ ነው (Hutchlson and Toress 1994)::

ተስፋዬ(1993) የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት አስፈላጊነትን እንደሚከተለው ያስገነዝባሉ፡፡

1 .የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ለመምህሩ የትምህርቱን ቅደም ተከተል ለመወሰንና በማቅረብ መነሻውንና መድረሻውን ለመጠቆምና ምን ማድረግ እንዳለበት በማመላከት ትምህርቱን ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲያስተምር እገዛ ያደርጋል፡፡

2. የተለያዩ ጉዳዮችን በማቅረብ የሚፈጸሙ ስራዎችን በመወሰን፣ ተማሪው የተማረውን በተግባር እንዲገልጽ ዕድል በመስጠት መምህሩም ሆነ ተማሪው ሊገነዘቡት የሚችሉትን ይዘቶች በማቅረብ ትምህርቱ አስደሳች እንዲሆን ያደርጋል፡፡

3. የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት በቋንቋ ትምህርት ዘርፎች መካከል ያለውን ቅንጅት አጥጋቢ በሆነ ስልት ለማጣመር ያግዛል፡፡ ይህም የቋንቋውን ክሂሎች በተመጣጠነ ደረጃ ለማስተማር ከማገዛቸውም በላይ የቃላት አመራረጥን፣ የአገባብ ስርዓትን፣ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምን፣ የአጻጻፍ ውበትን ወዘተ የሚያጠቃልሉ በመሆናቸው ጉልህ እገዛ ያደርጋሉ፡፡

ከላይ ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለው የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት መርሃ ትምህርቱን መሰረት አድርገው የታቀዱ የመማር ማስተማር ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ገለጻዎችን መልመጃዎችንና ምሳሌዎችን ወዘተ አካትተው በመያዛቸው ተማሪዎች የታለመውን የትምህርት ግብዓት እንዲያገኙና ባገኙትም የቋንቋ ግብዓት አማካይነት ቋንቋውን እንዲለማምዱና ብቁ እንዲሆኑ የሚያስችል ሰነድ መሆኑን ነው፡፡

## 2.3 የጽሕፈት ክሂል ትምህርት አላማ

የጽሕፈት ክሂል ትምህርት አላማ ተማሪዎችን በመማር ማስተማር ሂደት ሀሳባችን በፅሁፍ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመለዋወጥ፣ የህብረተሰቡን ባህል ወግንና ልማዶችን ከትውልድ ወደ ትውልድ በፅሁፍ ለማሸጋገር የተማሪዎችን የአስተሳሰብ አድማስን ለማስፋትና ሀሳባቸውን በጽሁፍ መልክ እዲገልፁ ማድረግ ነው፡፡

Ur(1996) የጽሕፈት ክሂል ትምህርት አላማ በመርህ ደረጃ ሀሳብን በተለያዩ መንገዶች በመግለፅ ለአንባቢ መልእክት በፅሁፍ ማስተላለፍ ነው፡፡ ሀሳብን ወይም መልእክትን ለማስተላፍ ቀላሉና አስፈላጊው ክሂል የጽሕፈት ክሂል ነው፡፡ ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው አንድ ፀሀፊ የሚገለገልበትን የታላሚው ቋንቋ ትምህርት ይዘት ሀሳብን በፅሁፍ በሚገልፅበት ጊዜ የቋንቋውን የቃላት አጠቃቀም፣ የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም ወዘተ… በተገቢው ቦታ መጠቀማቸውን ለመለየት መጠቀም እንዳለብን እንረዳለን፡፡

በአጠቃላይ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘት አላማ በአንድ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የህብረተሰቡን ባህል ወግንና ልማዶችን ከትውልድ ወደ ትውልድ በፅሁፍ ለማስተላለፍ፣ የንግግር ችሎታ ለማዳበር ተማሪዎች በክሂል የራሳቸውን እውቀት ለማዳበር ተማሪዎችን ከመሰሎቻቸው ጋር በቀላሉ የመግባባት ብቃታቸውን ለማዳበር ሳይንሳዊ ግኝቶችን ለተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ለማድረስና የተለያዩ መረጃዎችን ለመቀበልና ለመፃፍ እንደሚጠቅም የሚያሳይነው፡፡

## 2.4 የጽሕፈት ክሂል ይዘት ምንነት

የጽሕፈት ክሂል ይዘት በአንድ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የምንጠቀምበትን የታላሚው ቋንቋ ትምህርት ተግባራትን ወይም አላማ ለማሳካት የምንገለገልበት ስርአት ነው፡፡ Hedg(1991) የጽሕፈት ክሂል ይዘት ለመማሪያነት የሚቀርበብትና ተግባራዊ የሚሆኑትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተግባራትን እንደ

ትምህርቱ ፍላጎት የክፍል ደረጃና የማስተማሪያ ዘዴ የተለያዩ መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡ Raimes (1991) የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች የምንላቸው በቋንቋ የእለት ተእለት አገልግሎት ላይ ያተኩራሉ፡፡ ተማሪዎች በጥንድና በቡድን በመሆን ልዩ ልዩ ትእምርታዊ ተግባራትን እንዲያከናውኑና እንዲማሩ ያበረታታል፡፡

ከዚህ ሃሳብ የምንረዳው የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ዝንባሌን ይፋ ያወጣል፡፡ እንዱሁም የተማሪዎችን በትምህርት ቤት ውስጥ ያላቸው ማህበራዊ አመለካከትን ያሰፋል፡፡ በዚህም ስርአሰትና አጠቃቀም ተማሪዎችን የጽሕፈት ክሂል በማሳደግ በኩል ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ በመሆኑም የጽሕፈት ክሂል ይዘት የሚዳብረው በመፃፍ ልምምድ በመሆኑ ፅህፈትን የመለማመድ ተግባራትን ወይም አደረጃጀትን ትኩረት የሚሻ ተግባር ነው፡፡

## 2.5 የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች ምርጫ

ከአንድ ቋንቋ አካላት ውስጥ የተወሰኑት ተመርጠው በይዘትነት እንደሚቀርቡ ቀደም ተብሎ ተገልጸዋል፡ የመማሪያ መጽሕፍ አዘገጃጀትም ለጽሕፈት የሚውሉትን ይዘቶች በተማሪውደረጃ አመጣጥነው እንዴት መምረጥ እንዳለባቸው ሊያጠኑ ይገባቸዋል:: የቋንቋ ትምህርት ይዘት ምርጫ ስለቋንቋ ባህርይና ትምህርት ባለ ንድፈ ሐሳባዊ አመለካከት ይወሰናል (Nunan 1988)፡፡ በዚህም መሰረት የትኞቹ የቋንቋ አካላት ለየትኞቹ ተማሪዎች ይቅረቡላቸው የሚለውን ለመመለስ የተማሪዎቹን የቋንቋ ችሎታ፣ፍላጎት፣ዝንባሌና እውቀት በጥንቃቄ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ በጽፈት ክሂል ረገድም ስለ ጽህፈት ትምህርትና ባህርይ አስቀድሞ መገንዘብ ይዘቶቹን በመወሰን ረገድ የሚጫወተው ሚና ቀላል ሆኖ አይገመትም፡፡ አምደስላሴ ገብረክርስቶስ (1985፣69) ‹‹ይዘቶች ሲመረጡ የተማሪውን ውስጣዊ ጥንካሬ በመገንባት ለዓለምና በይበልጥም ለአካባቢው የሚኖረው አተያ የሚያሻሽሉት ላይ ማተኮር ያስፈልጋል፡፡›› በማለት የይዘት ምርጫ እልፍ ብሎ ማሰብን የሚጠይቅ ተግባር መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ ስለዚህ ለጽህፈት ክሂል የሚመረጡት ይዘቶችም ተማሪው በደረጃው ሐሳቡን በሚገባ ለመግለፅ የሚያስችሉት ሊሆኑ ይገባቸዋል፡፡

የትምህርት ይዘቶች ምርጫ የሚያስፈልገው የክሂሉን ትምህርት በማቅረብ ረገድ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ነው፡፡ የጽህፈት ክሂል የይዘቶች ሲመረጡም ከተማሪዎቹ ስሜትና ፍላጎት ጋር ያላቸው ስምረት፣ተግባራዊ ጠቀሜታቸው፣ ለመማር ያላቸው

አመቺነት፣ ከዓላማ ጋር ያላቸው ቁርኝትና ስፋት ጥልቀታቸው ሊመረምሩ ይገባቸዋል፡፡ ለበርካታ ምሁራን የጋራ የሆኑት የይዘት መምረጫ መስፈርቶች ተገቢነት አስፈላጊነት፣ዘላቂነት፣አስደሳችነትና ለመማር ያላቸው ምቹነት ናቸው (Cunningsworth 1995 ur 1996 Nutt!! 1983 Tyle 1949)::

በመቀጠል እነዚህን ለይዘት መምረጫ መስፈርቶች ከጽህፈት ክሂል ይዘቶች አኳያ ለማየት እንሞክር፡፡

2.5.1 **ተገቢነት/appropratness/** ለክሂሉ የተነደፈውን ዓላማ ግብ በማስመታት የባህርይና የአሰራር ለውጥ ለማስገኘት መለማመጃ እንዲሆንኑ ማድረግ ተገቢነትን ያሳያል፡፡ አንድን ይዘት ተማሪው በተግባር ሊያውለው የሚችለው ካልሆነ ዋጋቢስ ነው፡፡ የፊደላትን ቅርፅ ለይቶ ላላወቀ ተማሪ አንቀፅ እንዲፅፍ የሚያመለክት ይዘት ተገቢነት የሌለው የይዘት ምርጫ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪው በፅህፈት ሊኖረው የሚገባውን መግባባት ያሳዱጉለት ዘንድ የሚመረጡለት ይዘቶች ከችሎታውና ከትምህርቱ ዓላማ ጋር የተገናዘቡ መሆን አለባቸው፡፡

2.5.2 **አስፈላጊነት፣** የሚመረጠው ይዘት ተማሪው እንዲያውቀው የተፈለገውን ነገር ለመጨበጥ ያስችለዋልን የሚለውን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ የተማሪው ጹሑፋዊ ተግባቦት እንዳይዳከም ተዘውትረው ጥቅም ላይ የሚውለው የቋንቋው መዋቅራዊ ቅርፆችና ቃላት ላይ ትኩረት ማድረግን ይጠይቃል፡፡

2.5.3 **ዘላቂነት፣** የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች ተማሪው ከክፍል ውጪም ሊለማመድባቸው የሚያስችሉት መሆን አለባቸው፡፡ ይህም ይዘቶቹ ለረዥም ጊዜ ሊያገለግሉ መቻላቸው ዘላቂነትን እንደሚያሳይ ያስገነዝባል፡፡ በፅህፈት ትምህርት የስርኣተ ነጥቦች አጠቃቀም ዘላቂነት ላለው ይዘት እንደ ምሳሌ ሊጠቀስ ይችላል፡፡ ስርኣተ ነጥቦች ቋሚነት ያላቸው የጽሁፍ ውስጥ የተለያየ ግልጋሎት የሚሰጡ ምልክቶች ናቸው(Hrriss 1993 Pincas 1982) ::

2.5.4 **አስደሳችነት፣** ተማሪው የሚቀርቡለት ይዘቶች በአካባቢው የሚያገኛቸውና ለህይወትም ቅርበት ያላቸው ከሆኑበት ሊያስደስቱት ይችላሉ፡፡ በአንፃሩም ከገጠመኞቹ የራቁ ከሆኑ ግራ የሚያጋቡት ይሆናሉ፡፡ የይዘቶች አስደሳችነት ከተተግባሪነት ጋርም ተያያዥነት መሆን አለበት፡፡በጽሒፈት ክሂል የደብዳቤ አፃፃፍን ሲለማመድ የብዕር ጓደኛ አፍርቶ ሀሳብ የመለዋወጥ እድል ካገኘ መግባባት አቅሙ ይጎለብታል፡፡ በውጤቱም እየረካበትና እየተበረታታ ይሄዳል፡፡ ተማሪው ሊሞክረው የሚችለው ይዘት ስለሚያስደስተው እርካታን ያስገኝለታል፡፡ ስለዚህ አስደሳችነት የተሪውን ችግር በማቃለልና እቅዱንም በማሟላት ስሜቱን የሚስበውን በመምረጥ ላይ የተመሰረተ መስፈርት መሆኑ መገንዘብ ይቻላል (Cunnings Worth 1983 Tyler 1949)::

2.5.5 **ለመማር ያላቸው አመቺነት፣** (Learnabity) የትምህርት ይዘቶች ሲመርጡ የቀደሙትን መሰረት ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ ይህም ትምህርቱን ለተማሪው ትርጉም አዘል ያደርግለታል፡፡ ከፊደላት ቅርፅ ለመለየት በኋላ የቃላት አመሰራረት ከዚያም የአረፍተ ነገር አወቃቀር እያለ የሚያስጉዝ ይዘት ለመማር አመቺነት ያለው ነው፡፡ ከላይ ለማሳየት የተሞከሩት የይዘት መምረጫ መስፈርቶች አንዱ ለአንዱ ድጋፍ የሚሰጡ ናቸው፡፡ ምክንያቱም በአላማው የታሰቡ የባህርይ ለውጥ የሚገኘው በሁሉም መጣመር ስለሆነ ነው፡፡ ይህ መስፈርቶች የመረጡ የጽሒፈት ክሂል ይዘቶች አላማ ከግብ ለማድረስ እንዴት ተደራጅተው መቅረብ አለባቸው? ለሚለው ጥያቄ ደግሞ ከዚህ ቀጥሎ መልስ ለመስጠት ይሞክራል፡፡

## 2.6 በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሒፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት

በእያንዳንዱ የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሒፈት ክሂል ትምህርት የይዘቶች አደረጃጀት በሚደረጉበት ጊዜ የሚቀርቡትን ይዘቶች ለትምህርቱ አቀባበል ምቹ አድርገው ማቀናበር ያስፈልጋቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት እያንዳንዱ የቋንቋ

ትምህርት የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች የቀደመውን የክፍል ደረጃ መሰረት በማድረግ መደራጀት ይኖርባቸዋል፡፡

Taba(1962) እንደሚገልፀው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የትምህርቱ ይዘቶች ቅንጅታዊ ውጤት ማስገኘት ይቻል ዘንድ እርስበራሳቸው ሊደራጁ ይገባል፡፡ አደረጃጀታቸውም ተዋረዳዊና ጎናዊ ግንኙነቱን የጠበቀ እንዲሆን ያስፈልጋል ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ አያይዞም Cunningsworth(1995) የአንድ የቋንቋ ትምህርት አላማ ከግብ ለማድረስ በጥንቃቄ የተመረጡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ለተማሪዎቹ የሚቀርብበት ደረጃና ይዘቶቹም የሚኖራቸው ስፋትና ጥልቀት እንዲሁም ከሌሎች የትምህርት ይዘቶች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አደረጃጀታቸው ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ተጨባጭ ከሆነው ወደ አልሆነው መደራጀት ይኖርበታል ሲል ያብራራል፡፡

ከእነዚህ ሀሳቦች የምንረዳው በየክፍል ደረጃቸው የሚቀርቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች እርስ በርሳቸው ተደጋግፈው መሄድ አለባቸው፡፡ ይህም የሚደራጁት የትምህርት ይዘቶች ውጤታማ እንዲሆኑ በመጀመሪያው የክፍል ደረጃ የሚሰጠው የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከቀጣዮቹ የክፍል ደረጃዎች ከሚሰጡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ጋር ተያያዥነትና ተለጣጣቂነት በስፋትና በጥልቀት መመልከት አስፈላጊ መሆኑን የሚያብራሩና የሚገልፁ ናቸው፡፡ በቋንቋ መማሪያ መፅሀፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት የይዘቶች አደረጃጀት ሲባል የትምህርቱን አላማ ለማስፈፀም በቋንቋ መማሪያ መፅሀፍት ውስጥ የሚቀርቡትን ይዘቶች ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው የተማሪውን የቅደም እውቀት፣ የትምህርት ደረጃ፣ ባህላዊ ዳራ በሚመጥን መልኩ መደራጀት አለባቸው፡፡

የይዘት አደራጃጀት ሲባል በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚቀርበው የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘት አደረጃጀት እንዴት ባለ ቅደም ተከተል መቅረብ እንዳለበት፣ የትኛው ከየትኛው መቅደም እንዳለበት፣ የትኛው ደግሞ መከተል እንዳለበት የሚያመለክትነው፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ ተተኳሪ የሚሆነው የአደረጃጀት ስልት የይዘት ተዋረዳዊ ግንኙነት የሚያሳይ ነው፡፡ ጎናዊ ግንኙነት ደግሞ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያለውን ትስርር የሚያመለክት ጉዳይ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ትኩረት ውጪ ነው፡፡ በጥናቱ ውስጥ ተተኳሪ ወደ ሚሆነው አደረጃጀት ስንመለስ Cunningsworth (1995)

እንደገለፁት ተዋረዳዊ(ቀጥተኛ)ግንኙነት የሚባለው በሚዘጋጀው የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚኖረውን የይዘት አደረጃጀትና ቅደም ተከትልን የሚያመለክት ከመሆኑም በተጨማሪ ቀደም ሲል በተማሩትና በሚቀጥለው የክፍል ደረጃ በሚማሩት የይዘት አደረጃጀት ላይ ያተኩራል፡፡ ይህም በቋንቋ ትምህርት ይዘቶች መካከል ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት እንዲኖር ያደርጋል በማለት ይገልፃሉ፡፡ Nunan(1988) እና Yelden(1987) አገላለፅ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ሲባሉ የትምህርቱን ይዘቶች ከቀላል ወደ ከባድ የሚደራጁበትን ስልት የሚያሳይ እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡ ይህ ጥናት የሚከተሉትን የይዘቶች አደረጃጀት ስልቶች ወይም መስፈርቶች ይይዛል፡፡ እነርሱም ተከታታይነት፣ ተለጣጣቂነት፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ናቸው፡፡ እነዚህም እንደ ሚከተለው በቅደም ተከተል እንመለከታለን፡፡

### 2.6.1 ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት

በዚህ የአደረጃጀት ስልት የምንጠቀምበትን ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለፃ አይቀርብም ፡፡በመጀመሪያ ደረጃ የቋንቋውን ህግጋት ሊጠቁሙ የሚችሉ የተለያዩ ምሳሌዎችን ለተማሪዎች ይቀርባሉ፡፡ ተማሪዎችም የሚቀርብላቸውን ምሳሌዎች በመመርመር የቋንቋውን ህግጋት ምን ሊሆኑ እንደሚችል ይገምታሉ፡፡ Freeman (1991) እና Waod (1995) እንደ ሚገልፁት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ማለት በአግባቡ የተመረጡ ምሳሌዎች አደራጅቶ በማቅረብ የተሰጣቸውን ተግባራት ወይም መልመጃዎች ከሰሩ በኋላ የቋንቋን ህግጋት በራሳቸው ጥረት እንዲደርሱበት የሚያደርግ ነው ሲሉ ይገልፃሉ፡፡ አክለውም Cunningsworth(1995) ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ስልት የህፃናትን የአፍ መፍቻ ቋንቋ አለማመድ የተከተለና ተፈጥሮአዊ እንደሆነ ይገልፃል፡፡

### 2.6.2 ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት

ይህ የአደረጃጀት ስልት በመማር ማስተማር ዙሪያ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተማሪዎች ስለሚማሩት የቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ አደረጃጀት የሚቀርብበት ነው፡፡ ከአደረጃጀቱም በመነሳት ለተማሪዎች በመጀመሪያ ስለ ቋንቋው ህግመጠነኛ ገለፃ ከተሰጠ በኋላ በዚህ መነሻነት እንዲማሩ ወደ ተፈለገው የቋንቋ ትምህርት ይዘት እንዲሸጋገሩ የሚደረግበት ነው፡፡

እንደ Freeman(1991) እና Waod(1995) እንደ ሚገልፁት በዚህ የአደረጃጀት ስልት

ተማሪዎች ስለሚማሩት ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለፃ ይደረግላቸዋል፡፡ ከገለፃው በመነሳት ህግጋቱን በተግባር ላይ ወይም በተግባቦት ለማዋል ይሞከራል። ይህም መሆኑ ተማሪዎች የቋንቋ ህግጋት በፍጥነትና በቀላል እንዲረዷቸው ያርጋቸዋል ይላል። ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው በአንደ የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚቀርቡ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀቶች በሚደራጁበት ወቅት የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ መሰረት በማድረግ ከአጠቃላይ የቋንቋ ህግጋት በመነሳት ወደ ዝርዝር የቋንቋ ህግጋት በሚሄድ መልኩ መደራጀት እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው።

በአጠቃላይ ከላይ ከተነሱት አራት የአደረጃጀት ስልቶች ውስጥ አንደኛው የተሻለ ነው፤ ሌላኛው ደግሞ አይደለም ብሎ ማበላለጥ የሚቻል አይደለም። ምክንያቱም ሁልንም የቀረቡት የአደረጃጀት ስልቶች በውስጣቸው የየራሳቸው የሆነ አስተዋፅኦ ስላላቸው አንዳቸው ለአንዳቸው መስረትም ጭምር ስለሆኑ ተነጣጥለው መደራጀት እንዳለባቸው ተመልክተናል። በመሆኑም አንዱ የሌላኛውን ክፍተተ እንደሚሞላ በመገንዘብ የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘት በሚደራጅበት ወቅት አራቱንም እንደ አስፈላጊነቱ መጠቀምና ማካተት ተገቢ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን በአንድ ክፍል ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የተለያየ ዳራና ፍላጎት ያላቸው ስለሚሆኑ የተለያዩ የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች እንዳ አስፈላጊነቱ አራቱንም የአደረጃጀት ስልቶች ተካተው ሊቀርቡ ይገባል።

### 2.6.3 ተከታታይነት

‹‹ተከታታይነት ማለት በአንድ የትምህርት አይነት እና የክፍል ደረጃ ውስጥ የሚካተቱ ይዘቶች እድገት እየሰፉና እየተደጋገሙ የሚመጡ መሆናቸው የሚመለከት ነው፡፡›› ሲል ተስፋዬ (1981፣42) ያስቀምጣል። አክለውም Cunningsworth (1995)፣ Freeman (1991) አገላለፅ ተከታታይነት በአንድ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በምን አይነት ቅደም ተከተል ሊደራጁና ከተማሪዎች እድገት አንፃር ስፍትና ጥልቀት እየጨመሩ ሊቀርቡ እንደ ሚገባ የሚያሳይ ነው፡፡ በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ እያንዳንዱን የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ተደጋግመው መምጣታቸው ጠቀሜታ አላቸው ፡፡ይህም ማለት አንድ አዲስ የቋንቋ ትምህርት ይዘት አንድ ጊዜ ብቻ መቅረቡ በቂ አይደለም፡፡ ይልቁንም ተማሪዎች ይዘትን በተለያዩ ምእራፎችና በተለያዩ አውዶች ውስጥ ሊያስገኙት ይገባል፡፡ ይህም ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ይዘቱን በሚገባ እንዲረዱትና እንዲያውቁት ያስችላል። ድግግሞሹ ደግሞ ለጽሕፈት ክሂል ይዘቶች ጠቀሜታ አለው፡፡ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በአንድ ጊዜ ቢቀርቡ

የትምህርቱ ይዘቶች ሊይያያዙ ይችላሉ ሲሉ ያስቀምጣሉ:: ተሻለ (2001) አበበ (1990)ን ጠቅሶ ሲያብራራ ተከታተይነት የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ እንደሚከተለው አስፍሮታል፡፡ ‹‹ተከታታይነት ማለት ተዋረዳዊ ቅንብርን እንደ መስፈርት የሚከተል ክፍል ሲሆን፤ይህም የሚያሳየው ተከታታይነት ሊቋረጥ የማይችል ዋና የስርተ ትምህርት ክፍል መሆኑን ነው››፡፡

ከእነዚህ ሀሳቦች የምንረዳው በመጀመሪያውና በቀጣዩ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ የሚገኙትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተከታታይነት ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ ተከታታይነት በአንድ የክፍል ደረጃ ውስጥ በየምእራፉ ተከታታይነት መኖሩንና አንደኛው የክፍል ደረጃ ከቀጣዩ የክፍል ደረጃ የይዘት እንዲሁም ከአንድ የትምህርት ይዘት ወደ ሚቀጥለው የትምህርት ይዘት በተደጋጋሚ ሳይቆረጡ ተከታታይነትና በቅደም ተከተል መደራጀት እንዳለባቸው የምንመለከትበት የአደረጃጀት ስልት ነው፡፡

### 2.6.4 ተለጣጣቂነት

ይዘቶች ያላቸውን መደጋገምና መተሳሰር የሚያሳይ ነው፡፡ እንዲሁም የትምህርት ይዘቶች ይህ መስፈርት ከተከታታይነት ጋር የሚዛመድ ቢሆንም የሚለይበት ባህሪም አለው፡፡ ይኸውም በስርአተ ትምህርት ውስጥ የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች በየደረጃው ስፋትና ጥልቀት እያገኙ እንዲሄድ የሚመራ ነው፡፡ ተለጣጣቂነት የአንድን ጉዳይ ተደጋጋሚነት ሳይሆን የጉዳዩን እያደገ ወይም እየሰፋ መሄድን የሚጠይቅ ነው ሲል ተስፋዬ (1981፣41-42) ይገልፃል፡፡ ከዚህም ሀሳብ የምንረዳው በእያንዳንዱ የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትና መርሀ ትምህርት ውስጥ የሚቀርቡትን የትምህርት ያላቸውን ስፋት፣ ጥልቀትና እድገት ማስተዋልን የሚጠይቅ የአደረጃጀት መስፈርት ሲሆን አንድ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በሚዘጋጅበት ወቅት ይህንን መስፍርት ከሞላ ጎደል አሟልቶ መደራጀት ይኖርበታል የሚል ነው፡፡

የትምህርቱን ይዘቶች ቀጣይነት ባለው መልኩ ሳይቆራረጡ እርስ በእርስ ተሳስረውመደራጀት እንደለባቸው የሚያሳዩ እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡ ይህም ተለጣጣቂነታቸው ወይም ቀጣይነታቸው ከክፍል ወደ ክፍል እያደጉና ጥልቀታቸውም እየጨመሩ የሚሄድ መሆን ይኖርባቸዋል በማለት ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡ Nunan(1988) እና Yelden(1987) አገላለፅ ደግሞ Freeman(1991) እንደሚገልፁት ተለጣጣቂነት በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ተለጣጣቂነት የሚለው ፅንሰ ሀሳብ

የሚያመለክተው በመጀመሪያ እና በቀጣዩ የክፍል ደረጃ የሚገቡ ትምህርት ይዘቶችን ቅደም ተከተል የሚያሳዩ እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ተለጣጣቂነት ሲባል በአንድ የክፍል ደረጃም ሆነ በቀጣዩ የተለያዩ የክፍል ደረጃዎች በማስተማሪያነት የሚደራጁ የጽሕፈትሰ ክሂል ትምህርት ይዘቶች አንደ የክፍል ተማሪዎች ደረጃ እና የግንዛቤ አቅም አንፃር መደራጀት እንዳለባቸው የሚገልፁ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ተለጣጣቂነት ስንል የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችን ከአንደ የክፍል ደረጃ ወደ ቀጣዩ የክፍል ደረጃ በቀጣይነት መደራጀታቸውና መቅረባቸው የምናይበት ነው፡፡ ይህም በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚቀርቡትን የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች ሳይቆራረጡ ተለጣጣቂነት በሆነ ሁኔታእርስ በራሳቸው ተሳስረው እንዲደራጁ ያግዛቸዋል፡፡ በእንዲህ ያለ ሁኔታ መደራጀቱ ደግሞ ተማሪዎች በመማሪያ መፅህፍት ውስጥ ያሉትን ወይም የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችን ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲጠቀሟቸው ማድረጉ ትልቅ  አስተዋፅኦ ይሰጣል፡፡

## 2.6 የቀደምት ጥናታዊ ፅሁፎች ቅኝት

በዚህ የጥናት ክፍል የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትን በርእሰ ጉዳይነት ተያይዘው የተሰሩ እና ከርእሰ ጉዳዩ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው የምርምር ስራዎችን ይዳሰሳል፡፡ ስለሆነም የቀደምት ጥናዊ ፅሁፎች ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር ያላቸውን ቀጥተኛ ግንኙነትና ተዛምዶ ለማሳየት ይሞከራል፡፡ ስለሆነም ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት ያላቸው የቀደምት ጥናታዊ ፅሁፎች የጥናቱ ርእስ፣አላማ፣የአጠናን ዘዴና የተደረሰበት ማጠቃለያ በአጭሩ እንደሚከተለው ይቀርባል ፡፡

ተሻለ (2005) ‹‹የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ክሂሎችን፣ ይዘቶችን፣ መልመጃዎችን፤ አቀራረብና አደረጃጀት፡፡›› በሚል ርእስ አቅርቧል፡፡ የጥናቱ አላማ በ2004ዓ.ም በተዘጋጀው የቋንቋ መማሪያ መጻሐፍ ውስጥ የተካተቱትን አራቱ የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት መተንተን ነው፡፡ በጥናቱ የተገኘው ግኝት የሚያመለክተው የክሂሎች ይዘቶች እና መልመጃዎች አቀራረብ ለመማር ማስተማሩ ሂደትም ሆነ ለተማሪዎቹ የክሂል ልምምድ አመቺ መሆናቸው የሚያሳይና የተማሪዎችን ዳራዊ እውቀት ከግንዛቤ ያስገቡ የቋንቋ ክሂሎች መልመጃዎች ያካተቱ መሆኑን የሚገልፅ ጥናት ነው፡፡ በጥናቱ ወቅት ለታዩት ችግሮች የተሰጡ የተለያዩ የመፍትሄ ሀሳቦች የክሂሎችና የይዘት አደረጃጀታቸው መሰረት ያደረጉ መልመጃዎች ክብድትና ቅለት ደረጃ መቅረባቸው የሚያሳይ ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት ከተሻለ

ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር የሚመሳሰለው የሁለቱም ጥናቶች መሰረት በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡ የቋንቋ ክሂሎች አደረጃጀት ላይ ማትኮራቸውና የሁለቱም ጥናቶች የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሰነድ ፍተሻና ቃለ መጠይቅ መጠቀማቸው ተመሳሳይ ያደርጋቸዋል፡፡

የተሻለ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ያለው መሰረታዊ ልዩነት የተሻለ ጥናት በአራቱንም የቋንቋ ክሂሎች መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት የሚዳስስ ጥናት ሲሆን ይህ ጥናት ግን በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀትን በፅፅር መፈተሽ ይሆናል፡፡ የተሻለ ጥናት ለዘጠነኛ ክፍል ብቻ የተዘጋጀውን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ብቻ ሲያተኩር ይህ ጥናት ግን በዘጠነኛ እና በአስርኛ ክፍል ማተኮሩ እንዲሁም የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ላይ ብቻ ማተኮሩ ጥናቱ ልዩነት ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም ጥናቶቹ ከሚጠኑበት ከጥናቱ ተጠኚዎች መጠን፤ ከሚያጠኑት የክፍል ደረጃ፤ ከመጻሐፍቶቹ አዲስነት ና ከጊዜ አንፃር ሰፊ ልዩነት አላቸው፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ የተሻለ ጥናት ቀደም ባሉት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያተኮረ ሲሆን ዋና ትኩረቱም የአማርኛ ቋንቋ ክሂሎች፤ ይዘትንና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት የሚመለከት ሲሆን ይህ ጥናት ግን በአዲሱ በ9ኛእና በ10ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ላይ ማትኮሩ እና ጥናቱ ንፅፅራዊ መሆኑ ከተሻለ ጥናት ይለየዋል፡፡

ፅጌ (1992) ‹‹ለፅሀፈት ክሂል የተመረጡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እንዴት ተደራጅተዋል፡፡›› በሚል ርእስ በአዲስ አበባ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ (5ኛ-8ኛ) ክፍል በተዘጋጁት በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ላይ የይዘት ትንተናና ግምገማ አካሂደዋል ፡፡ በጥናታቸው የደረሱበት ማጠቃለያ በአራቱም ክፍሎች የፅህፈት ክሂል ይዘቶችን አስምልክቶ የቀረበውን የተለጣጣቂነት መስፈርት በአግባቡ ስራ ላይ አለመዋልንና ለዚህም አብይ ምክንያት የሆነው ይዘቶቹ የተማሪዎችን ችሎታ የሚመጥኑ ሆነው ያለመመረጣቸው ጉዳይ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡››

ይህ ጥናት ከፅጌ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር የሚመሳሰለው የሁለቱንም ጥናቶች በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀት ላይ ማተኮረቸውና ሁለቱም ሰነድ ፍተሻ የመረጃ መሰብሰቢያ አድርገው መጠቀማቸው ያመሳስላቸዋል ፡፡

ሌላው ደግሞ የፅጌ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ያለው ልዩነት የፅጌ ጥናት (5ኛ-8ኛ) ክፍል የተዘጋጀውን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ላይ ብቻ ሲያተኩር ይህ ጥናት ግን በአዲሱ

በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ላይ ማተኮሩ እና ጥናቱ ንፅፅራዊ ጥናት መሆኑ ነው። በተጨማሪም ጥናቶቹ ከጥናት ቦታቸው ከተጠኝዎች መጠን ከሚጠኑበት የክፍል ደረጃ፤ ከመጽሐፍቶቹ አዲስነት ና ከሚጠኑበት ጊዜ አንፃር ሰፊ ልዩነት አለው።

ሰይድ (1993) ‹‹በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘትና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ-ዘድ ትግበራ ግምገማ።›› በሚል ርእስ በሰባት የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ጥናታቸውን አካሂደዋል። በጥናታቸው የደረሱበት ማጠቃለያም ተማሪዎች ፅህፈትን በተግባር በማለማመድ ሂደት የማስተማሪያ ዘዴ አለመታየቱን በመማር ማስተማር ሂደቱም የሚቀርቡት ይዘቶችና ክንውኖች ለደረጃው በመርሀ ትምህርቱ ከቀረቡት ዝቅ ያለ መሆናቸውንና የፅሁፍ ተግባቦትን ለመፍጠር የሚያስችል አለመሆናቸውን አመልክተዋል። ይህ ጥናት ከሰይድ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ሁለቱንም ጥናቶች በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘት ላይ ማትኮራቸው ሲሆን የስይድ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ያለው ልዩነት ደግሞ የሰይድ ጥናት በዘጠነኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ የሚመለከትና በአዲስ አበባ በተመረጡ በሰባት ትምህርት ቤቶች ላይ የተደረገ ጥናት ሲሆን ይህ ጥናት ግን በአዲሶቹ በዘጠነኛ እና በአስረኛ ክፍል ለሙከራ ስራ ላይ በዋሉት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት የይዘቶች አደረጃጀት  መፈተሽ በሚል ርእስ በመማሪያ መጻህፍቶቹ ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ከአደረጃጀት መስፈርቶች አንፃር በንፅፅር የሚፈትሽና የሚገመግም በመሆኑ ሰፊ ልዩነት አላቸው።

በአጠቃላይ የተሻለ ጥናት የፅጌና የሰይድ ጥናቶች በቀደሙት ጊዜያት አገልግሎት ላይ በነበሩ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ላይ ያተኮሩ ናቸው። የተሻለ ጥናት ትኩርት በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በቀረቡ የአራቱንም የቋንቋ ክሂል መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት የሚዳስስ ሲሆን የፅጌ ጥናት ትኩረት (ከ5ኛ- 8ኛ) ክፍል ለፅህፈት ክሂል የተቀመጡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እንዴት ተደራጅተዋል በሚል የቀረበ ሲሆን የሰይድ ጥናት ትኩረት ደግሞ በዘጠነኛ ክፍል በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ይዘትና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ትግበራ ግምገማ የሚመለከቱ ሲሆኑ በእነዚህም ጥናቶች የታዩት የይዘት አደረጃጀት ችግሮች በዘጠነኛ እና በአስርኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ላይ የይዘቶች አደረጃጀት ተመሳሳይ ችግሮች መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ እንደ መነሻ ሆነው ያገለግላሉ። ነገር ግን ይህ ጥናት በዋናነት በአዲሶቹ በ9ኛ እና በ10ኛ ክፍል

በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት የይዘቶች አደረጃጀት ላይ ያተኮረና መማሪያ መጽሐፍቶቹ በንፅፅር የሚገመግም በመሆኑ ከላይ ከቀረቡት ጥናቶች እንደሚለይ መገንዘብ ይቻላል። በተጨማሪም መጽሐፉ አዲስ በመሆኑና ከዚህ በፊት የተጠና ባለመሆኑ ተሻሽሎ የቀረበው መጻህፍ አደረጃጀት ምን እንደሚመስል ይመለከታል።

# ምዕራፍ ሶስት፤የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በአዲሱ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሕፍት ውስጥ የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ንፅፅራዊ ግምገማ ማድረግ ነው። አጥኚው መረጃውን ሰብስቦ ያጠናው ቅይጥ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በዋናነት መጠናዊ ምርምር ዘዴን እና በደጋፊነት አይነታዊ ምርምር ዘዴን ስራ ላይ ውሏል።

በዚህ ጥናት አጥኚው ቅይጥ የምርምር ዘዴን የተጠቀመበት ምክንያት የሚተነተነው በቁጥር መረጃ ትንተናና በገለፃ ስለሆነ ነው። በመሆኑም መጠናዊ ምርምር በቁጥር የመረጃ ትንተና ላይ የተመሰረተ የምርምር አይነት በመሆኑ አጥኚውም በቁጥር ለሚገልጸው የመረጃ ትንተና አመች ሆኖ ስላገኘው ሊመርጠው ችሏል። ሌላው በደጋፊነት አይነታዊ ምርምር የተመረጠበት ምክንያት ደግሞ አይነታዊ ምርምር በቁጥር መረጃ ትንተና ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በገለፃ ላይ የሚያተኩር ነው። ስለዚህ በቁጥር ከሚተነተነው ውጭ ያለ መረጃ አይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን አቀራረቡ ግን በገላጭ ንድፍ ላይ የተመሰረተ ነው። በመሆኑም አጥኚው ቅይጥ የምርምር ዘዴን የሚከተለውን የ Cresswell,(2009) እና የያለው (2001) የምርምር መጻሕፍት ለጥናቱ መነሻ ግብዓትነት ተጠቅሟል።

በመሆኑም የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችን ከይዘት አደረጃጀት መርሆች አንጻር በመተንተን ከቃለ መጠይቅ ከሚገኙ ውጤቶች ጋር አቀናጅቶ በመገምገም ጥናቱ ይዞት ለተነሳው ጥያቄዎች መልስ ለመፈለግ ጥረት ተደርጓል።

## 3.2 የጥናቱ የመረጃ ምንጮች

በዚህ ጥናት የሚካተቱ ተጠኚዎች ከላይ በተጠቀሱት የክፍል ደረጃዎች መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች አደረጃጀትና በዚህ ደረጃ ላይ የአማርኛ ቋንቋን መማሪያ መጻሕፍት የሚያዘጋጁ አዘጋጆች ወይም አስማምቶዎች ናቸው። በመሆኑም አጥኚው ካለበት የጊዜ፣ የጉልበትና የገንዘብ ውስንነት የተነሳ በጥቂት ምንጮች ላይ ለመወሰን

ተገዶዋል፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት ዋነኛው የመረጃ ምንጭ የሚሆኑት የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል አዲሶቹ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የጽሕፈት ትምህርት ክሂል ይዘቶች ሲሆኑ፤

በተጨማሪም በመረጃ ምንጭነት የሚካተቱ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የመምሩ መምሪያ፣የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል መርሀ-ትምህርት የመማሪያ መጻህፍት እና የሲለበስ አዘገጃጀት ኮርስ በመረጃ ምንጭነት ያገለገሉ ናቸው፡፡

## 3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

በዚህ ጥናት የሚካተቱ ተጠኚዎች በ(9ኛእና 10ኛ) የክፍል ደረጃዎች ውስጥ የሚገኙትን በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ይዘቶችና የመማሪያ መጻሕሰፍት አዘጋጆች ናቸው፡፡

### 3.3.1 የክፍል ደረጃ፤መማሪያ መጻሕፍት ናሙና አመራረጥ ዘዴ

ለዚህ ጥናት የተመረጡት መማሪያ መጻሕፍት አዲሶቹ የ9ኛእና የ10ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ናቸው ፡፡በዚህም መሰረት አጠቃላይ የጥናቱ አካላይ ብዛት ሁለት ሲሆኑ እነዚህም የ9ኛእና የ10ኛ የክፍል ደረጃዎችና የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት በአላማ ተኮር የንሞና ዘዴ ተመርጧል፡፡ በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትም ሆኑ የ9ኛ እና የ10ኛ የክፍል ደረጃ በተከታታይነት የተወሰደበት ምክንያት በጽሕፈትክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ያላቸውን ቀጣይነት፣ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት በአግባቡ ለመገምገም ያስችላል ተብሎ ስለታሰበ ነው፡፡

### 3.3.2 የመጻሕፍት አዘጋጆች ናሙና አመራረጥ ዘዴ

በጥናቱ ተተኳሪ እርከን ያሉት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ብዛት ሁለት ናቸው፡፡ በእነዚህ በሁለቱም የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት የተለያዩ ሁለት ሁለት አዘጋጆች እንደ ክፍሎቹ ቅደም ተከተላቸው የመማሪያ መጻሕፍት አደራጅተው አዘጋጅተዋቸዋል፡፡ በመሆኑም በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን የመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች ማለትም (የ9ኛእና የ10ኛ) ክፍል የአዘጋጆቹ ስም መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ቢኖሩም አድራሻቻው ማወቅና ማግኘት የተቻለው ሁለቱን አዘጋጆች ብቻ በጥናቱ ውስጥ ተሳታፊ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ከእነዚንም ውስጥ ሁለቱም የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አዘጋጅ ናቸው፡፡ የሁለቱም አድራሻ ጅማ ዩኒቨርሲቲ በመምህርነት የሚያስተምሩ ናቸው፡፡ አጥኚው ሁለቱንም በማግኘት በቃለ መጠይቁ ለማሳተፍ የቻለ ሲሆን 10ኛ ክፍል ሁለቱም

የመማሪያ መጽሐፍት አዘጋጆች በተለያ ምክንያቶች (በቦታ ርቀት አድራሻ ለውጥ) ምክንያት ማግኘት ስላልተቻለ በቃለ መጠይቁ ማሳተፍ አልተቻለም፡፡

## 3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

አንድ ጥናት ለማካሄድ ስንነሳ መረጃ መሰብሰብ ዋናና በደንብ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት አጥኚ ጥናቱን ከግብ ለማድረስ የሚጠቀምባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሰነድ ፍተሻና ቃለ መጠየቅ ናቸው፡፡

### 3.4.1 ሰነድ ፍተሻ

በዚህ ጥናት አጥኚው ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አድርጎ ከሚጠቀምባቸው ውስጥ አንዱ ሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የሚፈተሹትም መዛግብቶች በ2015 ዓ.ም ለሙከራ ስራ ተግባር ላይ የዋሉት የ9ኛእና የ10ኛ የክፍል ደረጃዎች በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል የይዘቶች አደረጃጀት መገምገም ነው፡፡ በዚህም መስረት ጥናቱ የሚካሄደው ከላይ በክለሳ ድርሳናት የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ንድፈ ሀሳብ ተመርኩዞ ሲሆን እነዚህን ንድፈ ሀሳቦች መሰረት በማድረግ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ለመለየት ተሞክሯል፡፡

### 3.4.2 ቃለ መጠይቅ

ሁለተኛው ጥናቱ መረጃ የሚሰበሰብበት መንገድ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ ቃለ መጠይቅ በዚህ ጥናት እንደ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያነት የሚያገለግል ሳይሆን በድጋፍ ሰጭነት የሚያገለግል ነው፤ ምክንያቱም በቃለ መጠይቅ የሚሰበሰብ መረጃ የተሟላ ስለማይሆን በዋና የመረጃ ምንጭነት ሚያገለግለው የተተኳሪዎቹ የክፍል ደረጃ መጽሕፍቶች ናቸው፡፡ በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ አይነት አጥኚው የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት በየደረጃቸው ከሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች በቃለ መጠይቅ አማካኝነት ምላሻቸውን በመውሰድ የፍተሻውን ውጤት የሚያጠናክርበት ነው፡፡ በመሆኑም ለአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆችም በተተኳሪው የክፍል ደረጃዎች ውስጥ የጽሕፈተ ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትን የሚመለከቱ አምስት ጥያቄዎች በአጥኚው ተዘጋጅቶ በአማካሪው ከተገመገሙ በኋላ በተሰጠው አስተያየት መሰረት ተሻሽለው ለመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች በቃለ መጠይቅ መልክ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

## 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

የዚህ ጥናት አላማ በ2015 ዓ.ም ለሙከራ ስራ ላይ በዋሉት በአዲሶቹ (የ9ኛ እና የ10ኛ) ክፍል ለሚማሩ ተማሪዎች የተዘጋጁ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል የይዘቶች አደረጃጀት መፈተሽ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የሚሰበሰቡትን እንደየመረጃዎቹ ባህሪ አይነታዊና መጠናዊ በሆነ መንገድ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

### 3.5.1 የሰነድ ፍተሻ አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት ውስጥ አጥኚው የሚፈትሻቸው ሰነዶች የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል የተዘጋጁ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች አደጃጀትን በመለየት በአይነታዊ የአተናተን ዘዴ በመጠቀም በተተኳሪቹ መማሪያ መፅሀፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ከንድፈ ሀሳቦች አንፃር ተተንትኗል፡፡

### 3.5.2 የቃለ መጠይቅ አተናተን ዘዴ

በዘህ ጥናት ቃለ መጠይቅ የሚካሄደው አጥኚው አስቀድሞ ባዘጋጃቸው ጥያቄዎች ስለሚሆን ጥያቄዎቹ ቃለ መጠይቅ በሚያደርግባቸው በእያንዳንዱ ተተኳሪ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች ወይም አስማምቶዎች በቃለ መጠይቅ የተገኙት ምላሾችን በመጠቀም በገለፃ መልክ ትንተናውን ለማጠናከር ተሞክሯል፡፡ በአጠቃላይ በሁለቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደየ መረጃዎቹ ባህሪይ አይነታዊ (Qualitative) እና መጠናዊ (Quantitative) በሆነ መንገድ ተተንትኗል፡፡ መጠናዊ የምርም ዘዴን መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት አጥኚው በተጠቀሱት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ላይ ጥናት በሚያካሄድበት ወቅት ለግምገማው በተዘጋጁት መስፈርቶች አማካኝነት የተሰበሰቡትን መረጃዎች የቁጥር መለኪያ በመስጠት በመቶኛ ተንትኖ ለማስቀመጥ አማራጭ ዘዴ በመሆኑ እና በአይነት በአይነት በማድረግ ለመተንተን አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ሲሆን አይነታዊ የምርምር ዘዴን ደግሞ ለጥናቱ አጋዥ የመረጃ ምንጭ ከሆኑት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሕፍት አዘጋጆች በቃለ መጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰቡት መረጃዎች በገለፃና ማብራሪያ ለማስቀመጥ አማራጭ ዘዴ በመሆኑ ነው፡፡

# ምእራፍ አራት፤የመረጃ ትንተና እና የውጤት  ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአዲሶቹ የዘጠነኛ እና የአስርኛ ክፍል (የ9ኛእና የ10ኛ) ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት መገምገም ነው፡፡ ስለሆነም በእነዚህ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ በሰነ ዘዴ ፍተሻ የተገኙት መረጃዎች በክለሳ ድርሳን ከቀረበው ንድፈ ሀሳቦች አንፃር መተንተን ነው፡፡ በጥናቱ ውጤት ትንተና የተገኘው መረጃ በጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም ትንተናውን በቃለ መጠይቅ በተገኙት ምለሾች ለማጠናከር ተሞክሯል፡፡ በመጀመሪያ ስለቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጣዊና ውጫዊ ገፅታ አጠር ያለ ቅኝት መመልከት ያስፈልጋል፡፡

## 4.1 የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አጠቃላይ ቅኝት

የዘጠነኛ እና የአስረኛ (9ኛእና 10ኛ) የክፍል ደረጃ እርከን ውስጥ የሚገኙትን የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት  በ2015 ዓ.ም ለሙከራ ስራ ላይ የዋሉት የአማርኛ ቋንቋ  መማሪያ መጻሕፍት ናቸው፡፡ በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት ሆነ አደረጃጀት ወቅት ትኩረት ከሚያሻቸው ነገሮች መካከል የመማሪያ መፃህፍት ውስጣዊና ውጫዊ ገፅታዎች ዋነኞቹ ናቸው፡፡ በውስጣዊ ገፅታ ውስጥ ከሚመደቡትና በዝግጅት ውቅት ጥንቃቄን ከሚሹት ክፍሎች ውስጥ የመፃህፍቶቹን ሽፋን፤ጥንካሬና ውበት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች አንፃር የሁለቱንም ተተኳሪዎች መማሪያ መፃህፍት ሽፋን በቀላሉ ሊበላሹ ወይም ሊቀደዱ በማይችሉ አይነት የተሰሩ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ሽፋኑ ጠንከር ባለ ክላሴር ወረቀት የተዘጋጀ በመሆኑ ነው፡፡ እንዲሁም ላያቸው ላይ የሚገኙትን መረጃዎች አራቱንም አይነት የቋንቋ ክሂሎች በሚያምርና በሚስብ መልኩ በስእል መልክ የሚገልጹ በመሆናቸው የተማሪዎችን እይታ ይማርካሉ፡፡
አጥኚው በጥናቱ ወቅት ይህንኑ ጉዳዮች የሚያሳዩ በርካታ ነገሮች ተመልክቷ፡፡ ማለትም ከመማሪያ መጻሕፍቱ ሽፋን ቀጥሎ ባሉት የመጀመሪያ ገፆቻቸው ላይም መፃህፍት ለዘጠነኛ እና ለአስረኛ ክፍል እንደተዘጋጁ የስርአተ ትምህርት ዝግጅት ክፍል አዘጋጆችና ኤዲተሮች ሙሉ ስም በግልፅ መስፈሩን ተመልክቷል፡፡
ሌላኛውና ሁለተኛው በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ዝግጅት ሆነ አደረጃጀት ወቅት ትኩረት ከሚያሻቸው ነገሮች መካከል የመማሪያ መፃህፍት ውስጣዊ ገፅታ ነው፡፡ በዚህ ውስጣዊ ገፅታ ውስጥም ከሚካተቱ የመማሪያ መፃህፍቱ መግቢያ፤የይዘት ማውጫ፤የታተመበት ቦታና የመጻሕፍቶች አጠራረዝ ናቸው፡፡ የመማሪያ መጻሕፍት መግቢያ በሚመለከት በአዘጋጁ ተዘጋጅቶ የሚቀርብና ስለዝግጅቱ በቂ የሆነ ጥቆማ የሚቀርብበት ክፍል ሲሆን በተተኳሪዎቹ

የክፍል ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍትን መግቢያ ላይ የቀረቡትን መረጃዎች በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ተካተው የሚገኙትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች የሚዳስሱና የቋንቋ ትምህርቶቹን አጠቃላይ አላማዎች በትክክል ያስቀመጡ ናቸው ለማለት ይቻላል፡፡ የይዘት ማውጫ በተመለከተ ደግሞ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በቀረቡት የቋንቋ ክሂሎች ስር የተጠቀሱት ተግባራት የያዙ ሲሆኑ በእነዚህ የቋንቋ ክሂሎች ተግባራት ዝርዝር ከቀረቡበት ገፅ ስር የተገናዘቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም ተፈላጊዎቹን ተግባራት በቀላሉ ለማውጣትና ለማየት የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ከህትመት ጥራት ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚገባው ነጥብ በየምዕራፉና በየትምህርት ክፍሉ የሚፃፉ ርዕሶችና ንዑሳን ርዕሶች የሚቀርቡበት የአፃፃፍ ስልት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የተተኳሪዎቹ መማሪያ መፃህፍት ይህንን መስፈርት ያሟሉ ናቸው ማለት ያስችላል፡፡

ሰንጠረዥ 1. የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አጠቃላይ ቅኝት

| ተ/ቁ | የመማሪያ መጻህፍት ጠቅላላ መረጃ | የተግባራት ብዛት በየክፍሉ | |
|---|---|---|---|
| | | 9ኛ ክፍል | 10ኛ ክፍል |
| 1 | ለሙከራ ተግባር ላይ የዋሉበት ዘመን | 2015 | 2015 |
| 2 | የገፆች ብዛት (መጠን) | 108 | 109 |
| 3 | ያሉ ምዕራፎች ብዛት | 10 | 10 |
| 4 | የመፃህፍቶቹ ዋጋ | 20 | 20 |

### 4.1.1 በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን ተግባራት ብዛት

በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የተግባራት ይዘቶች በንዑስ የክፍል ደረጃዎች ምን እንደሚመስሉ መቃኘትና የአጠቃላዩ የትምህርት ይዘቶች በሚመለከት ቀጥሎ የቀረበውን ሰንጠረዥ እንመልከት፡፡

ሰንጠረዥ 2. በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የተግባራት ብዛት

| ተ/ | የተግባራት አይነት | የክፍል ደረጃ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 9ኛ ክፍል | | 10ኛ ክፍል | | | |
| | | ተግባራቱ የያዙትን ዑሳን ክፍል | | ተግባራቱ የያዙት ንዑሳን ክፍል | | የተግባራት ጠቅላላ ድምር | |
| | | ቁጥር | መቶኛ | ቁጥር | መቶኛ | ቁጥር | መቶኛ |
| 1 | የማንበብ ክሂል | 39 | 24.4 | 11 | 9 | 50 | 15.1 |
| 2 | የመፃፍ ክሂል | 27 | 25.3 | 35 | 28 | 62 | 32.3 |
| 3 | የማዳመጥ ክሂል | 32 | 20 | 8 | 6 | 40 | 12.0 |
| 4 | የመናገር ክሂል | 21 | 13 | 44 | 35 | 65 | 19.6 |
| 5 | ቃላት | 25 | 16 | 20 | 16 | 45 | 13.6 |
| 6 | ሰዋሰው | 16 | 10 | 9 | 7.1 | 25 | 7.5 |
| | ድምር | 160 | 100% | 127 | 100% | 287 | 100% |

ከሰንጠረዥ 1 እና 2 የምንረዳው ጥናቱ ወደ ዋናው የጥናቱ ክፍል ከማለፉ በፊት በመግቢያው ላይ የስራኣተ ትምህርቱን መሰረታዊ መርሆች፤ከትምህርት ቤት ውጭ የተማሪዎችና የወላጆችን ትምህርታዊ ተግባራት እንዲሁም የመጽሐፉን የይዘት አደረጃጀት በማስተዋወቅ መጀመሩ በመረጃነተ ያገለግላል ተብሎ ባጥኚው ስለታመነባቸው ነው፡፡

### 4.1.2 በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ትንተና

sከላይ የዘጠነኛ እና የአስረኛ (የ9ኛ እና የ10ኛ) ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት አጠቃላይ ቅኝት በሚለው ርዕሰ ጉዳይ ስር እንደተገለፀው በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በርካታ የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች በተግባራትና በማብራሪያዎች መልክ እንደቀረቡ ተመልክቷል፡፡

የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቱን የሚጠናክሩበት ምሳሌዎች ጭምር በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ተካተው ቀርበዋል፡፡ ለምሳሌ፡- የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን መርጦ አንቀፅ መፃፍ፤ የተንደሉ ሀሳቦችን አሟልቶ መፃፍ፤ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ ያላቸውን አገባባዊና አውዳዊ ፍቺ መፃፍ፤የደብዳቤ አፃፃፍ መመሪያ መሰረት በማድረግ የስራና የግል ደብዳቤ መፃፍ፤ ግጥም መፃፍ፤ስርአተ ነጥብ በተገቢው ቦታ መጠቀም፤ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ላይ ማስታወሻ ወስዶ መፃፍ፤ስዋስዋዊ ስህተት ያለባቸው አረፍተ ነገሮች እንደገና አስተካክሎ መፃፍ ወዘተ የሚሉት ሲሆኑ እነዚህ በተለያዩ መልክ የቀረቡት የመፃፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶችም ከቃላት፣ሀረግ፣ አረፍተ ነገር ምስረታ እስከ አስተዋፅኦ /ቢጋር/ አዘጋጅቶ ሀሳብ አዘጋጅቶ መፃፍ ጀምሮ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች መርጦ ድርሰት እስከ መፃፍ ድረስ ያሉትን በርካታ የሚሆኑ የመፃፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶች አጠቃለው የያዙ ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህ የዘጠነኛ እና የአስረኛ የክፍል ደረጃዎች በሚገኙት በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ስርጭት መጠን ወይም ብዛት ቀጥሎ በሚቀርበው ሰንጠረዥ ሶስት (3) ላይ መመልከት ይቻላል፡፡

ሰንጠረዥ 3. በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ላይ የቀረቡት ተግባራት ብዛት

| ተ/ቁ | የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ዝርዝር ተግባራትን መጻፍ | የተግባራት ብዛት በየክፍሉ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 9ኛ ክፍል | | 10ኛ ክፍል | |
| | | ቁጥር | መቶኛ | ቁጥር | መቶኛ |
| 1 | የተዘበራረቁ ዐ.ነግሮች ዕንደገና አስተካክሎ መፃፍ | 1 | 3.7 | | |
| 2 | የደብዳቤ አፃፍፍ መመሪያ በመከተ የስራ/ማመልከቻና የግል ደብዳቤ መፃፍ | | | 2 | 3.7 |
| 3 | ቃላት በዐ.ነገር ውስጥ ያላቸውን አገባባዊና አውዳዊ ፍቺ መጻፍ | | | 2 | 3.7 |
| 4 | የተንደሉ ሀሳቦችን አማልቶ መፃፍ | 3 | 11.11 | 1 | 1.9 |
| 5 | የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዩችን መርጦ አንቀጽ መፃፍ | 3 | 11.11 | 3 | 5.6 |
| 6 | ሰዋሰዋዊ ስህተት ያለባቸው ዐረፍተ ነገሮች አስተካክሎ እንደገና መፃፍ | 3 | 11.11 | 3 | 5.6 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 7 | ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ተግባራት ላይ ማስታወሻ ወስዶ መፃፍ | 2 | 7.4 | 2 | 3.7 |
| 8 | ስርአተ ነጥብ በተገቢው ቦታ መፃፍ | 2 | 7.4 | | |
| 9 | ግጥምመፃፍ | | | 3 | 5.6 |
| 10 | የህይወት ታሪክ መፃፍ | | | 3 | 5.6 |
| 11 | ቢጋር በማዘጋጀት አመዛዛኝናገላጭ/አስረጅ ድርሰት መፃፍ | | | 3 | 5.6 |
| 12 | የተሰጠው ሀሳብ በምሣሌው መሰረት በጹሁፍ አበራርቶ መግለፅ | 3 | 11.11 | 2 | 3.7 |
| 13 | የዐ.ነገሮች ስልትን መሰረት በማድረግ ዐ.ነገር መፃፍ | 1 | 3.7 | 1 | 1.9 |
| 14 | ግጥምን ወደ ዝርው ቀይሮ መፃፍ | | | 1 | 1.9 |
| 15 | አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት በዐ.ነገር ውስጥ አስተካክሎ መፃፍ | | | 1 | 1.9 |
| 16 | የዐ.ነገር ተዋቃሪ ክፍሎች ለይቶ መፃፍ | 3 | 11.11 | 1 | 1.9 |
| 17 | ምሣሌያዊ አነጋገሮች የሚያስተላልፉትን መልእክት መፃፍ | 2 | 7.4 | | |
| 18 | የድርሰት አፃፃፍመመሪያ በመከተል ድርሰት መፃፍ | 3 | 11.11 | 4 | 7.4 |
| 19 | በቃል ውስጥ የሚገኙት ስረወ ቃሎችና ቅጥያዎች ለይቶ መፃፍ | 1 | 3.7 | 1 | 1.9 |
| 20 | በዐ.ነገር ውስጥ ስማዊ ና ግሳዊ ሀረግ ለይቶ መፃፍ | | | 1 | 1.9 |
| 21 | በመረጡት ርዕሰ ጉዳይ አጭር ልቦለድ መፃፍ | | | 2 | 3.7 |
| | ድምር | 27 | 100% | 35 | 100% |

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ ለመግለፅ እንደተሞከረው በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አይነቶች ዝርዝር ስንመለከት በተሰጠው ርዕሰ ጉዳይ ስር

ተዘበራርቀው የቀረቡ አረፍተ ነገሮችንና አንቀፆች እንደገና አስተካክሎ መፃፍ፤የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን መርጦ አንቀፅ መፃፍ፤የተጓደሉ ሀሳቦችን አሟልቶ መፃፍ፤ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ ያላቸውን አገባባዊና አውዳዊ ፍቺ መፃፍ፤የደብዳቤ አፃፃፍ መመሪያ መሰረት በማድረግ የስራና የግል ደብዳቤ መፃፍ፤ግጥም መፃፍ፤ስርአተ ነጥብ በተገቢው ቦታ መጠቀም፤ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ላይ ማስታወሻ ወስዶ መፃፍ፤በዐ.ነገር ውስጥ ስማዊ ና ግሳዊ ሀረግ ለይቶ መፃፍ፤በመረጡት ርዕሰ ጉዳይ አጭር ልቦለድ መፃፍ ስዋስዋዊ ስህተት ያለባቸው አረፍተ ነገሮች እንደገና አስተካክል መፃፍ ወዘተ የሚሉትን ያጠቃለሉ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ በተታኳሪዎቹ የክፍል ደረጃዎች መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ነክ ማብራሪያዎችና ምሳሌዎች ቀርበዋል

ሰንጠረዥ 4. በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ብዛትና መገኛ ገፅ ማብራሪያ

| ተ/ቁ | በቋንቋ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የሚገኙ በመፃፍ ክሂል ትምህርት ማብራሪያዎች ዝርዝር ይዘቶች | የክፍል ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 9ኛ ክፍል | | 10ኛ ክፍል | |
| | | ብዛት | መገኛ ገፅ | ብዛት | መገኛ ገፅ |
| 1 | የተዘበራረቁ ዐ.ነግሮች ዕንደገና አስተካክሎ መፃፍ | 1 | 89 | | |
| 2 | የደብዳቤ አፃፃፍ መመሪያ በመከትል የስራ/ማመልከቻና የግል ደብዳቤ መፃፍ | | | 2 | 11፣76 |
| 3 | ቃላት በዐ.ነገር ውስጥ ያላቸውን አገባባዊ ና አውዳዊ ፍቺ መፃፍ | | | 2 | 91 |
| 4 | የተጋደሉ ሀሳቦችን አማልቶ መፃፍ | 3 | 2፣26፣33 | 1 | 87 |
| 5 | የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዩችን መርጦ አንቀጽ መፃፍ | 3 | 17፣27፣89 | 3 | 21፣23፣96 |
| 6 | ሰዋሰዋዊ ስህተት ያለባቸው ዐረፍተ ነገሮች አስተካክሎ እንደገና መፃፍ | 3 | 38፣39፣48 | 3 | 38፣79 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 7 | ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ተግባራት ላይ ማስታወሻ ወስዶ መፃፍ | 2 | 77፣100 | 2 | 23፣67 |
| 8 | ስርአተ ነጥብ በተገቢው ቦታ መፃፍ | 2 | 68፣71 | | |
| 9 | ግጥምመፃፍ | | | 3 | 47፣84፣86 |
| 10 | የህይወት ታሪክ መፃፍ | | | 3 | 12፣76 |
| 11 | ቢጋር በማዘጋጀት አመዛዛኝናገላጭ/አስረጅ ድርሰት መፃፍ | | | 3 | 23፣96፣98 |
| 12 | የተሰጠው ሀሳብ በምሣሌው መሰረት በጹሁፍ አበራርቶ መግለፅ | 3 | 47፣54፣77 | 2 | 37፣59 |
| 13 | የዐ.ነገሮች ስልትን መሰረት በማድረግ ዐ.ነገር መፃፍ | 1 | 13 | 1 | 106 |
| 14 | ግጥምን ወደ ዝርው ቀይሮ መፃፍ | | | 1 | 89 |
| 15 | አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት በዐ.ነገር ውስጥ አስተካክሎ መፃፍ | | | 1 | 57 |
| 16 | የዐ.ነገር ተዋቃሪ ክፍሎች ለይቶ መፃፍ | 3 | 8፣28፣49፣ | 1 | 106 |
| 17 | ምሣሌያዊ አነጋገሮች የሚያስተላልፉትን መልእክት መፃፍ | 2 | .<br>16፣19 | | |
| 18 | የድርሰት አፃፃፍመመሪያ በመከተል ድርሰት መፃፍ | 3 | 56፣58፣59 | 4 | 37፣57፣67፣77 |
| 19 | በቃል ውስጥ የሚገኙት ስረወ ቃሎችና ቅጥያዎች ለይቶ መፃፍ | 1 | 91 | 1 | 91 |
| 20 | በዐ.ነገር ውስጥ ስማዊ ና ግሳዊ | | | 1 | 106 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሀረግ ለይቶ መፃፍ | | | | |
| 21 | በመረጡት ርዕሰ ጉዳይ አጭር ልበለድ መፃፍ | | | 2 | 47፣48 |
| | ድምር | 27 | | 35 | |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው በዘጠነኛ እና በአስረኛ (9ኛ-10ኛ) ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍ የተካተቱት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተግባራት ብዛትና መገኛ ገጾች ተለይተው ቀርበዋል፡፡

## 4.2 የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ምርጫ

የ9ኛና የ10ኛ ክፍል የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች የምርጫ መስፈርቶችን የጠበቁ መሆን አለመሆናችውን ለመለየት ከመጽሐፉ የተገኙ ይዘቶች ትንተናየቋንቋን ክፍሎች በሙሉ በአንድ ጊዜ ለትምህርነት ማቅረብ ስለማይቻል የተወሰኑትን መርጦ በተማሪው ደረጃ እየመጠኑ ማቅረብ የግድ ነው፡፡ ለብዙ ምሁራን የጋራ ሆነው የሚያገለግሉት የይዘት መምረጫ መስፈርቶችም ተገቢነት፣ አስፈላጊነት፣ ዘላቂነት፣ አስደሳችነትና ለመማር ያላቸው አመቺነት ናቸው (Yalden 1987 Cunningsworth 1984 Taba 1962 Tyler 1949)፡፡ የይዘቶች ተገቢነት የሚታየው ተማሪው በተግባር ሊያውለው ከመቻሉ አኳያ፣አስፈላጊነት ተዘውትሮ ጥቅም ላይ ከመዋሉ አኳያ፣ዘላቂነት ለረዥም ጊዜ ሊያገለግል ከመቻሉ ሰአኳያ፣አስደሳችነት በደረጃው ተጠቅሞበት በውጤቱ ከመበረታታት አኳያ፣ለመማር ያለው አመቺነት ደግሞ ከቀደመ እውቀቱ ጋር ለመዛመድ ከመቻሉ አኳያ ነው፡፡ በዚህ መሰረትለዚህ ክፍል የተመረጡት የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች ከመስፈርቶቹ አኳያ ሲታዩ ብቃታቸው በቂ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ምክንያቱም ተማሪው ሊሰራቸው የሚችላቸው ይዘቶች በብዛት በመሆናቸው ነው፡፡ በዚህም መሰረት ቃላትን፣ስርዓተ ነጥቦችን፣የደብዳቤን ቅርፅ ወዘተ የተመለከቱት ይዘቶች ተገቢ፣አስፈላጊ፣ዘላቂ፣አስደሳችና ለመማር ያላቸው አመቺነት የተጠበቁ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ የቀሩትንም ይዘቶች ለክፍሉ ተማሪ ተመጣጣኝ ከመሆናቸው የተነሳ በመስፈርቶቹ መሠረት የተመረጡ ናቸው ለማለት የሚያስደፍሩ ናቸው፡፡

(ለመረጃነት አባሪውን ይመልከቷል)

ይዘቶቹ የመምርጫ መስፈርቶችን የጠበቁ መሆን አለመሆናቸውን ለመለየት ለመምህራን ጥያቄ አልቀረበም ምክንያቱም ከመጻሕፉ ሙሉለሙሉ ወደ ትግበራ

ካለመግባት ጋር በተያያዘ በሁሉም የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ወደ ስራ ስላልገባ ለዚህ ጥያቄ ምላሽ አልተገኘለትም። ከመጽሐፉ አዘጋጆች የተሰጠው ምላሽ በተመለከተ በመምረጫ መስፈርቶች መሠረት የተመረጡ ይመስሉኛል ለማንኛውም መሠረት ያደረግነው መርሐ ትምህርቱን ነው።

የይዘት መምረጫ መስፈርቹን በተመለከተ ከመረጃዎቹ ለማየት እንደተቻለው በአግባቡ ስራ ላይ የዋሉ ሆነው ተገኝተዋል። ስለዚህ በመስፈርቶቹ አጠቃቀም ረገድ የሚታይ ችግር አልሆነም።

## *4.3 በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት*

ይህ ጥናት ከላይ በክለሳ ድርሳን ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የይዘቶች አደረጃጀት በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚቀርቡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እንዴት ባለ ቅደም ተከተል መደራጀት እንዳለባቸው፣ የትኛው ይዘት ከየትኛው መቅደምና መከተል እንዳለበት፤እንዲሁም እንዴት ባለ መንገድ ተደጋግመውና ጥልቀት እየጨመሩ መቅረብ እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው። በዚህም ይዘቶች ንም ያህል ተገቢ ቢሆኑ አደረጃጀታቸው ካላማረ የታሰበውን የባህርይ ለውጥ ሊያስገኙ እንደማይችሉ ምሁራን ያስረዳሉ (Cunningsworth 1984 Tyler 1949)።

ይህ ጥናት በዋናነት የሚጠቀምባቸው የአደረጃጀት መስፈርቶች ውስጥ ተከታታይነት፣ ተለጣጣቂነት፣ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝርና ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚሉትን የአደረጃጀት መርሆች ትኩረት የሚሰጣቸው ይሆናሉ።

### 4.3.1 የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከተከታታይነት አንፃር

ከላይ በክለሳ ድርሳን ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ተከታታይነት በአንድ ትምህርት አይነትና የክፍል ደረጃ ውስጥ የሚካተቱ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች እድገታቸው እየሰፋና እየተደጋገሙ የሚመጡ መሆናቸውን የሚያመላክት ፅንሰ ሀሳብ ነው። ይዘቶች አንድ ጊዜ ብቻ በመቅረባቸው ቋሚ ሊሆኑ ስለማይችሉ ተደጋግመው ሊቀርቡ ይገባቸዋል (Taba 1962 Tyler 1949)።

ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑትን የዘጠነኛ እና የአስረኛ (9ኛእና የ10ኛ) ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ምን አይነት ገፅታ እንዳላቸው ለመመልከት ተሞክሯል። ይህንን ሁኔታ ለማረጋገጥ ያመቸን ዘንድ የሁለቱም የዘጠነኛ እና የአስረኛ (9ኛእና 10ኛ) ክፍል በተከታታይ በየክፍል ደረጃቸው በሚገኙት በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ

የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተግባራት የድግግሞሽ ብዛት በቁጥር እና በመቶኛ የሚያሳዩ ሰንጠረዦች አንድ ባንድ እንመልከት፡፡

**ሀ. በዘጠነኛ ክፍል የቋንቋ መፃሕፍ መረጃ በተመለከተ**

ሰንጠረዥ 5. በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መፃሕፍ ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከተከታታይነት አንፃር የቀረቡት ተግባራት ብዛት

| ተ/ቁ | በመማሪ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የመፃፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶች ዝርዝር | የተግባራት ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | የተጓደሉ ሀሳቦችን አሟልቶ መፃፍ | 3 | 11.1 |
| 2 | የዐ.ነገር ተዋቃሪ ክፍሎች ለይቶ መፃፍ | 3 | 11.1 |
| 3 | የዐ.ነገሮች ስልትን መሰረት በማድረግ ዐ.ነገር መፃፍ | 1 | 3.7 |
| 4 | ምሣሌያዊ አነጋገሮች የሚያስተላልፉትን መልእክት መፃፍ | 2 | 7.4 |
| 5 | የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዩችን መርጦ አንቀጽ መፃፍ | 3 | 11.1 |
| 6 | ሰዋሰዋዊ ስህተት ያለባቸው ዐረፍተ ነገሮች አስተካክሎ እንደገና መፃፍ | 3 | 11.1 |
| 7 | የተሰጠው ሀሳብ በጹሁፍ አበራርቶ መግለፅ | 3 | 11.1 |
| 8 | ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ተግባራት ላይ ማስታወሻ ወስዶ መፃፍ | 2 | 7.4 |
| 9 | የድርሰት አፃፃፍመመሪያ በመከተል ድርሰት መፃፍ | 3 | 11.1 |
| 10 | ስርአተ ነጥብ በተገቢው ቦታ መፃፍ | 2 | 7.4 |
| 11 | የተዘበራረቁ ዐ.ነግሮች ዕንደገና አስተካክሎ መፃፍ | 1 | 3.7 |
| 12 | በቃል ውስጥ የሚገኙት ስረወ ቃሎችና ቅጥያዎች ለይቶ መፃፍ | 1 | 3.7 |
| | ድምር | 27 | 100% |

ከዚህ በላይ በሰንጠረዥ አምስት (5) እንደሚታየው በዘጠነኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከተካተቱት 12 የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች መካከል ሰዋሰዋዊ ስህተት ያለባቸው ዐረፍተ ነገሮች አስተካክሎ እንደገና መፃፍ፣የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዩችን መርጦ አንቀጽ መፃፍ፣የድርሰት አፃፃፍመመሪያ በመከተል ድርሰት መፃፍ፣የዐ.ነገር ተዋቃሪ ክፍሎች ለይቶ

መፃፍ፣የተሰጠው ሀሳብ በጹሁፍ አበራርቶ መግለፅ፣የተጓደሉ ሀሳቦችን አሟልቶ መፃፍ እያንዳንዳቸው ሶስት ሶስት ጊዜ ሆነው የቀረቡ ሲሆን ከአስራ ሁለት የመፃፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶች እነዚህን ስድስቶቹ ይዘቶች 66.6% ሽፋን ይዘው ቀርበዋል፡፡

ሌላው ደግሞ ከቀሪዎቹ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች መካከል ምሣሌያዊ አነጋገሮች የሚያስተላልፉትን መልእክት መፃፍ፣ስርአተ ነጥብ በተገቢው ቦታ መፃፍ፣ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ተግባራት ላይ ማስታወሻ ወስዶ መፃፍ እያንዳንዳቸው ሶስት ሶስት ጊዜ በመሆን ሲቀርቡ ከአስራ ሁለት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች እነዚህን ሁለቶቹ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች 22.2% ያህል እንደያዙ ያሳያል፡፡ የተቀሩት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ማለትም የተዘበራረቁ ዐ.ነግሮች እንደገና አስተካክሎ መፃፍ፤በቃል ውስጥ የሚገኙት ስረወ ቃሎችና ቅጥያዎች ለይቶ መፃፍ፣የዐ.ነገሮች ስልትን መሰረት በማድረግ ዐ.ነገር መፃፍ አንዳ አንድ ጊዜ ይዘው የቀረቡ ሲሆን እነዚህ ደግሞ ከአስራሁለት የመፃፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶች ውስጥ 11.1%ተከታታይነት የጎደላቸው የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች መሆናቸውን ያሳያሉ፡፡ ከዚህ በመነሳነት በመማሪያ መጻሐፉ ውስጥ ተካተው የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በአብዛኛው ተከታታይነታቸውን ጠብቀውና ተደጋግመው የቀረቡ መሆናቸው የሚያሳዩ ናቸው፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ ከፍተኛ መጠን ያላቸው የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችና ዝቅተኛ የድግግሞሽ መጠን ያላቸው የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አንጻር ልዩነት ይታያል፡፡ ይህም ደግሞ በዘጠነኛ የክፍል ደረጃ ውስጥ ተማሪዎች የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችን በተደጋጋሚ እንዳይለማመዷቸው ያደርጋሉ፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ በዘጠነኛ ክፍል 12 በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተደጋጋሚነት የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከምዕራፍ ምዕራፍ የይዘቶቹን ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ መቅረብ አለመቅረባቸው ለማረጋገጥ የሚከተለትን ምሳሌዎች በአስረጂነት እንመለከታለን፡፡

ተግባር 1. ቀጥሎ የተለያዩ የስራተ ነጥብ አይነቶች ቀርበዋል- እነዚህን ሥርዓተ ነጥቦች ከታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ በትክክለኛ ቦታቸው በማስገባት አረፍተ ነገሮቹን አስተካክላችሁ እንደገና ፃፉ፡፡ ለመስራት ከመሞከራችሁ በፊት ከታች ስለ ስርዓተ ነጥቦች አጠቃቀም የተሰጠውን ማስታወሻ ተመልከቱ፡፡

፣ ፤ ? ! ‹‹ ›› …

1. ከለምለም ማህፀንዋ የሚመነጨው ቡናዋ ውብ ሀሳቦች እያዋለደች ጅማ ገባች፡፡
2. ሰው ተሰብስቧል ውይይቱ ግን ገና አልተጀመረም፡፡

3. የስነጽሑፍ መምህርህ በዓሉ ግርማን ያፈራው ማህፀን የሆንኩትን እኔንናተመልከተኝ፡፡

4. አይሻ ጫልቱ በለጠችና ሐዋ የህዳስ ጓደኞች ናቸው፡፡

5. ወይኔ እኔ ኖሬ ቢሆን ኖሮ፡፡

(9ኛ ክፍል፣ገፅ-68)

ተግባር 2. የሚከተሉት ስርአተ ነጥቦችን በመጠቀም ዓረፍተ ነገሮችን ጽፋችሁ አቅርቡ፡፡

ሀ.፣ ለ. ፤ ሐ. ? መ. ! ሠ. ‹‹ ››

ተግባር 3. ስርዓተ ነጥቦች በፅፈት ውስጥ ካላቸው አገልግሎት ሁለቱን ብቻ ፃፉ፡፡

(9ኛ ክፍል፣ገፅ -68)

ግተባር-4. ቀጥሎ ከምንባቡ የተወሰዱ ሀረጎችና አረፍተነገሮች ቀርበዋል፡፡ ሀረጎችና አረፍተ ነገሮች ውስጥ የምታዩአቸውን ስህተቶች፤ በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ትክክለኛ ቅርፅ በመፈለግ እንደገና አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡

መምህራችሁ በአረፍተ ነገር ውስጥ ስለሚከሰቱ የስህተት አይነቶች ያስረዷችኋል፡፡

1. ለመቆጣጠር በጣም አዳጋች የሆነ ህመሞች ናቸው፡፡

2. የሰው ልጅ በመላው አለም እየተስፋፉ ሄዱ፡፡

3. ተላላፊ የሆኑ በሽታዎች በዛው ልክ ሊስፋፋ ችለዋል፡፡

(9ኛ ክፍል፣ገፅ -38)

ግተባር-5 ከታች የተሰጡትን የአገባብ ስህተት ያለባቸው አረፍተ ነገሮች በማስተካከል እንደገና ፃፏቸው፡፡

ምሳሌ ፡- ሀ. አዱኛ አንበሳውን ገደለው በጦር፡፡

ሲስተካከል ፡- አዱኛ አንበሳውን በጦር ገደለው፡፡

1.እኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውስ ሱስ ውስጥ ይከታል፡፡

2.ያስተሳሰብ ማንበብ አድማስን ያሰፋል፡፡

3.ታላቁ የህዳሴ ለኢትዮጵያ ግድብ ኩራት ነው፡፡

(9ኛ ክፍል፣ገፅ - 48)

በዚህ የክፍል ደረጃ ቀረበውን መማሪያ መጽሐፉ የተለያዩ ምዕራፍችና ገፆች ውስጥ በምሳሌነት የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አንዱን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘት በተለያየ ጊዜ ሲቀርብ ጥልቀቱንና ስፋቱን በጠበቀ ሁኔታ የቀረበ ነው ለማለት ያስችላል፡፡
ይህም ተማሪዎች በመጀመሪያው ተግባር ውስጥ ስርአተ ነጥብ ከቀረበላቸው አረፍተ ነገሮች ውስጥ በትክክለኛ ቦታቸው በማስገባት አረፍተ ነገሮቹን አስተካክለው እንደገና እንዲፅፉ ያዛል፡፡

በሁለተኛው ተግባር ውስጥ ስርአተ ነጥቦችን ተጠቅመው አረፍተ ነገሮችን እንዲፅፉ ያዛል፡፡ ሶስተኛው ደግሞ የስርአተ ነጥቦች ርዕስ ተሰጥቶዋቸው በፅሁፍ ውስጥ ያላቸው አገልግሎት ተማሪዎች በራሳቸው አገላለጽ እንዲፅፉ ለማድረግ የሚያዙ ተግባራት ቀርበዋል፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ በአራተኛው ተግባር ላይ ተማሪዎች በምንባብ ውስጥ የተወሰዱ ሀረጎች ና ዐ.ነገሮች ውስጥ ያለባቸው ስህተቶች በማስተካከል እንዲፅፉ ያዛል፡፡ አምስተኛው ተግባር ደግሞ ተማሪዎች ያገባብ ስህተት ያለባቸው አረፍተ ነገሮች በማስተካከል እንደገና እንዲፅፉ ያዛል፡፡ ይህ የአደረጃጀት ስልት  ስንመለከት በተተኳሪው የክፍል ደረጃ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀታቸው ጠብቀው የተደራጁ መሆኑን ያሳያል፡፡ በዚህ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡት ሌሎች የመፃፍ ክሂል ይዘቶችም ቢሆኑ በተለያዩ ገፆችና ምዕራፍች ውስጥ ተደጋግመው ከመቅረባቸው በተጨማሪ እየጨመሩ ወይም ከበድ እያሉ የሚሄዱ ናቸው፡፡

ከዚህ የክፍል ደረጃ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ከሆኑት ውስጥ አንዱ ‹‹የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከአደረጃጀት መስፈርቶች አንፃር እንዴት ተደራጁ? ማለትም ከተከታታይነት አንፃር?›› በማለት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ ‹‹አንድ ይዘት ተከታታይነት ከሌለው በተማሪዎች ዘንድ ሊረሳ ስለሚችል በመማሪያ መጽሐፍ የተለያዩ ምዕራፍች ውስጥ እንዲደጋገሙ ለማድረግ ሞክረናል፡፡ በዚህ የአደረጃጀት ስልት አንድ ይዘት ጥልቀት እንዲኖረው በተለያዩ ቀናት በተለያየ መንገድ ተደጋግመው ይቀርባል፡፡ ይህም ተማሪዎች አንድ ጊዜ ብቻ ተምረውት የሚያበቃ አይደለም፡፡ ለምሳሌ፡- አንድን ድርሰት እንዲፅፉ ብንፈልግ እነዚህ ተማሪዎች በአንድ ጊዜ ሀሳብን አመንጭተው ላይፅፉ ይችሉ ይሆናል፡፡ ይህም ተማሪዎቹ ቃላትን በትክክል መፃፍ የሚባል የአፃፃፍ ስርአት ቢኖር እሱም በተደጋጋሚ ይማሩታል፡፡ ስለዚህ የይዘቶቹ ድግግሞሽ ተመጣጣኝና እኩል በሆነ ሁኔታ ቀርቧል የሚል እምነት ቢኖረኝም መጠነኛ የሆኑ ክፍተቶች ሊኖሩ ይችላሉ›› የሚል ነው፡፡ እኚህ የመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ከሰጡት ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው የመጀመሪያው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተከታታይነት ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው መሆኑና በሁለተኛው ደረጃ ደግሞ የይዘቶች ተከታታይነት ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ የሚሔዱ መሆናቸው ነው፡፡ የመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ የሰጡት ምላሽ ብቻ ሳይሆን ከሰነድ ፍተሻው ውጤት መረዳት እንደተቻለው በዚህ የክፍል ደረጃ መማሪያ መጽሐፍ የተለያዩ ምዕራፍች ውስጥ የቀረቡትን የመፃፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት ይታይባቸዋል፡፡

በአጠቃላይ ከሁለቱንም የመረጃ ምንጮች የተገኘው ውጤት እንደሚያመላክተው በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተለያዩ ምዕራፍች ውስጥ ተደጋግምው የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በአብዛኛው ተከታታይነታቸው ጠብቀው የቀረቡ ሲሆኑ የይዘት ተከታታይነት ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ የሚሄዱ መሆናቸው የሚያመላክቱ ናቸው፡፡

## ለ. የአስረኛ ክፍል የቋንቋ መጽሐፍ መረጃ በተመለከተ

ሰንጠረዥ 6. በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከተከታታይነት አንፃር የቀረቡት ተግባራት ብዛት

| ተ/ቁ | በመማሪ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የመፃፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶች ዝርዝር | የተግባራት ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | የደብዳቤ አፃፃፍ መመሪያ በመከትል የስራ/ማመልከቻና የግል ደብዳቤ መፃፍ | 2 | 5.7 |
| 2 | የህይወት ታሪክ መፃፍ | 3 | 8.6 |
| 3 | የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዩችን መርጦ አንቀጽ መፃፍ | 3 | 8.6 |
| 4 | ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ተግባራት ላይ ማስታወሻ ወስዶ መፃፍ | 2 | 5.7 |
| 5 | ቢጋር በማዘጋጀት አመዛዛኝናገላጭ/አስረጅ ድርሰት መፃፍ | 3 | 5.6 |
| 6 | የተሰጠው ሀሳብ በምሣሌው መሰረት በጹሁፍ አበራርቶ መግለፅ | 2 | 5.7 |
| 7 | የድርሰት አፃፃፍመመሪያ በመከተል ድርሰት መፃፍ | 4 | 11.4 |
| 8 | ቃላት በዐ.ነገር ውስጥ ያላቸውን አገባባዊ ና አውዳዊ ፍቺ መፃፍ | 2 | 5.7 |
| 9 | ሰዋሰዋዊ ስህተት ያለባቸው ዐረፍተ ነገሮች አስተካክሎ እንደገና መፃፍ | 3 | 8.6 |
| 10 | የተጓደሉ ሀሳቦችን አማልቶ መፃፍ | 1 | 2.9 |
| 11 | በመረጡት ርዕሰ ጉዳይ አጭር ልቦለድ መፃፍ | 2 | 5.7 |
| 12 | አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት በዐ.ነገር ውስጥ አስተካክሎ | 1 | 2.9 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | መፃፍ | | |
| 13 | ግጥምመፃፍ | 3 | 8.6 |
| 14 | ግጥምን ወደ ዝርው ቀይሮ መፃፍ | 1 | 2.9 |
| 15 | በቃል ውስጥ የሚገኙት ስረወ ቃሎችና ቅጥያዎች ለይቶ መፃፍ | 1 | 2.9 |
| 16 | የዐ.ነገሮች ስልትን መሰረት በማድረግ ዐ.ነገር መፃፍ | 1 | 2.9 |
| 17 | በዐ.ነገር ውስጥ ስማዊ ና ግሳዊ ሀረግ ለይቶ መፃፍ | 1 | 2.9 |
| | ድምር | 35 | 100% |

በአስረኛ ክፈል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አስራ ሰባት የተለያዩ አይነት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች የቀረቡ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ በተለያዩ ምዕራፍች በከፈተኛ ደረጃ ተደጋግመው ከቀረቡት መካከል በተሰጠው ርዕሰ ጉዲይ ዙሪያ ድርሰት መፃፍ አራት ጊዜ፣የህይወት ታሪክ መፃፍ፣ግጥምመፃፍ፣ሰዋሰዋዊ ስህተት ያለባቸው ዐረፍተ ነገሮች አስተካክሎ እንደገና መፃፍ፣ ቢጋር በማዘጋጀት አመዛዛኝናገላጭ /አስረጅ ድርሰት መፃፍ ፣የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን መርጦ አንቀፅ መፃፍ እነዚህ እያንዳዳቸው ሶስት ሶስት ጊዜ ሆነው ቀርቧል፡፡ እነዚህ ይዘቶች ከአስራ ሰባት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ውስጥ 54.4% ሽፋን ይዘው ቀርቧል፡፡

ከቀሪዎቹ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች መካከል የደብዳቤ አፃፃፍ መመሪያ በመከተል የስራ /ማመልከቻና የግል ደብዳቤ መፃፍ፣ ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ተግባራት ላይ ማስታወሻ ወስዶ መፃፍ፣የተሰጠው ሀሳብ በምሣሌው መሰረት በጹሁፍ አበራርቶ መግለፅ፣ ቃላት በዐ.ነገር ውስጥ ያላቸውን አገባባዊ ና አውዳዊ ፍቺ መፃፍ፣ በመረጡት ርዕሰ ጉዳይ አጭር ልቦለድ መፃፍ እያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ጊዜ ተደጋግመው የቀረቡ ናቸው፡፡ እነዚህ ይዘቶች ከአስራ ሰባት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ውስጥ 28.5% ሽፋን ይዘው ቀርቧል፡፡ በዚህ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡት አስራ ሰባት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች መካከል 11 የሚሆኑት ከፍተኛ የሆነ ድግግሞሽ የቀረቡ ሲሆኑ የተቀሩት ደግሞ ከላይ ከቀረቡት የድግግሞሽ መጠን በታች ተደጋግመው የቀረቡ ናቸው፡፡

ሌላው ደግሞ የተጓደሉ ሀሳቦችን አማልቶ መፃፍ፣ አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት በዐ.ነገር ውስጥ አስተካክሎ መፃፍ፣ግጥምን ወደ ዝርው ቀይሮ መፃፍ፣በቃል ውስጥ የሚገኙት ስረወ ቃሎችና ቅጥያዎች ለይቶ መፃፍ፣የዐ.ነገሮች ስልትን መሰረት በማድረግ ዐ.ነገር መፃፍ፣

በዐ.ነገር ውስጥ ስማዊ ና ግሳዊ ሀረግ ለይቶ  መፃፍ እያንዳንዳቸው አንዳ አንድ ጊዜ ብቻ የቀረቡ ሲሆኑ እነዚህ ደግሞ አስራ ሰባት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ውስጥ 17.4% ተከታታይነት የጎደላቸው የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች መሆናቸው ያሳያል፡፡ ከፍተኛ መጠን ድግግሞሽ ያላቸው የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችና ዝቅተኛ መጠን ድግግሞሽ ያላቸው የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች መካከል ያለው የድግግሞሽ መጠን ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡

በዚህ መማሪያ መጸሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ሁሉንም ይዘቶች እኩል የድግግሞሽ መጠን አላቸው ብሎ ማሰብ ባይቻልም በተወሰነ መልኩ ተደጋግመው የቀረቡ 11 የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች መኖራቸው ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ ለመመልከት ተችሏል፡፡ ይህም ማለት በተተኳሪው የክፍል ደረጃ መማሪያ መጸሐፍ ውስጥ ተካተው የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተከታታይነታቸውን ጠብቀውና ተደጋግመው የቀረቡ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተደጋግመው የተካተቱት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችም ከአንደ ገፅ ወደ ሚቀጥለው ገፅ እንዲሁም ከአንድ ምእራፍ ወደ ሚቀጥለው ምእራፍና ክፍል ስፋት፣ጥልቀትና ክብደት እየጨመሩ መቅረብ አለመቅረባቸው ለማወቅ ይቻል ዘንድ ከመማሪያ መጸሐፉ በምሳሌነት የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

ተግባር 1. ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት አድርጉና በኢሜል መልዕክት መላክና በፖስታ መልዕክት መላክ አስመልክቶ መረጃዎች ከድረ ገፆች በመፈለግ በሁለቱ መካከል ያለውን ተመሳስሎ በማንሳት ከአንድ ገፅ ያልበለጠ አመዛዛኝ ድርሰት ጽፋችሁ  አሳዩ፡፡

(10ኛ ክፍል፤ገፅ 23)

ተግባር 2. ከተዘረዘሩት ርእሶች መካከል አንዱን መርጣችሁ ከ150 ቃላት ባልበለጠ ተራኪ፣ ስእላዊ፣ አስረጅ ወይም አመዛዛኝ ድርሰት ፃፉ፡፡

(10ኛ ክፍል ፤ገፅ 77)

ተግባር3. ርዕስ በመምረጥ፣ቢጋር በመንደፍ፣ ማርቀቅ፣መፃፍ፣ማደት፣እንደገናመፃፍ፣የሚሉ ተከተሎችን በመጠበቅ በመረጣችሁት ርዕስ አንቀፅ ፃፉ፡፡

(10ኛ ክፍል ፤ገፅ 57)

ተግባር 4. ከላይ ከምዕራፉ የቀረበውን የልቦለድ ምንባብ ጭብጦች/መልዕክቶች አሳጥራችሁ በሁለት አንቀጽ ፃፈ፡፡

(10ኛ ክፍል፤ገፅ 47)

ተግባር 5. የምዕራፍ ስድስት ባህላዊ ክንውኖች የሚለውን ምንባብ ዋናውን ጭብጥ አሳጥራችሁ ፃፉ፡፡

(10ኛ ክፍል፤ገፅ 66)

ከዚህ በላይ የቀረቡት ምሳሌዎች ውስጥ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በጽሕፈት ክሂል ትምህርት የቀረቡት ይዘቶች የመጀመሪያው ተግባር ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት አድርጉና በኢሜል መልዕክት መላክና በፖስታ መልዕክት መላክ አስመልክቶ መረጃዎች ከድረ ገፆች በመፈለግ በሁለቱ መካከል ያለውን ተመሳስሎ በማንሳት ከአንድ ገፅ ያልበለጠ አመዛዛኝ ድርሰት እንዲጽፉ ያዛል፡፡ ሁለተኛው ተግባር ከተዘረዘሩት ርሶች መካከል አንዱን መርጣችሁ ከ150 ቃላት ባልበለጠ ተራኪ፣ስእላዊ፣አስረጅ ወይም አመዛዛኝ ድርሰት እንዲፅፉ ያዛል፡፡ ሶስተኛው ተግባር ርዕስ በመምረጥ፣ቢጋር በመንደፍ፣ለማርቀቅ፣መፃፍ፣ ማደት፣እንደገናመፃፍ፣የሚሉ ቅደም ተከተሎችን በመጠበቅ በመረጡት ርዕስ አንቀፅ እንዲፅፉ የሚያዙ ሲሆኑ፡፡ አራተኛውና አምስተኛው ተግባር ደግሞ የተሰጣቸውን ምንባብ ሊያስተላልፈው የፈለገውን መልዕክት አሳጥረው እንዲፅፉ የሚያዙ ናቸው፡፡ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በተለያዩ ምዕራፍችና ገፆች በምሳሌነት የተካተቱት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተግባራት መረዳት እንደሚቻለው ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ተግባራት ተደጋግመው መምጣታቸውን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው ተግባራት ተደጋግመው መምጣታቸው የመማሪያ መጽሐፉን ተከታታይነት ለመጠበቅ ታስቦ የተደረገ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በዚህ የክፍል ደረጃ መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተመሳሳይነት ካላቸው ይዘቶች መካከል ከአቀራረባቸውም ሆነ ከክብደት አንፃር ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ ይህም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት እየጨሩ የመሔድ ሁኔታ ይታይባቸዋል፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ በመማሪያ መጽሐፉ አዘጋጅነት ከተካተቱት ሁለት የመማሪያ መጽሐፉ አዘጋጆች መካከል በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም የአድራሻ ለውጥ በማድረግ እና በቦታ ርቀት ምክንያት ማግኘት ስላልተቻለ አንዳቸውንም በቃለ መጠይቁ ማሳተፍ አልተቻለም፡፡

### 4.3.2 የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከተለጣጣቂነት አንፃር

በክለሳ ድርሳን ለመግለፅ እንደተሞከረው ተለጣጣቂነት በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚቀርቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች እያደጉና እየሰፉ ተደጋጋሚነት /ተለጣጣቂነት

በሆነ መንገድ እርስ በርስ ተሳስረው የሚደራጁበት መስፈርት ነው። በዚህ ጥናት በተተኳሪዎቹ የክፍል ደረጃ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ምን ያህልቹ እድገታቸው ጠብቀው እንደተደራጁ ነው። ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት ተተኳሪ በሆኑት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችን ተለጣጣቂነት አስመልክቶ ያላቸውን ገፅታ በሚከተለው መልኩ ለመዳስስ ተሞክሯል።

ከሰንጠረዥ ዘጠኝ መገንዘብ እንደሚቻለው ከዘጠነኛ እስከ አስረኛ ክፍል ባሉት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የተለያዩ አይነት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ይገኛሉ። በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ከተካተቱት አጠቃላይ ይዘቶች 21 መካከል ሰድስቶቹ (6) 16.7% ያህልቹን በተተኳሪዎቹ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ ያለምንም መቆራረጥ ተለጣጥቀው ቀርበዋል። በሌላ መልኩ ደግሞ ከአጠቃላዩ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች መካከል 30ዎቹ 83.3% ያህሎቹ የተለያዩ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በተተኳሪዎቹ የክፍል ደረጃዎች መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ተለጣጥቀው የመቅረብ ችግር /ድክመት/ እንዳለባቸው ያሳያሉ።

ከሰንጠረዥ 7. የዘጠነኛ እና የአስረኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች የስርጭት መጠን ከተለጣጣቂነት አንጻር፤

√ ተለጣጣቂነት በአንድ የክፍል ደረጃ ወይም በተከታታይ የክፍል ደረጃዎች የሚቀርብ የትምህርት ይዘት መጀመሪያ ከቀረበው የትምህርት ይዘት ተነስቶ ነገር ግን ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ መምጣትን የሚመለከት እንደሆነ በክለሳ ድርሳናት ክፍል ተጠቁሟል።

| ተ/ቁ | የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ዝርዝር ተግባራትን መፃፍ | የተግባራት ብዛት በየክፍሉ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 9ኛ ክፍል | | 10ኛ ክፍል | |
| | | ቁጥር | መቶኛ | ቁጥር | መቶኛ |
| 1 | የተዘበራረቁ ዐ.ነግሮች ዕንደገና አስተካክሎ መፃፍ | 1 | 3.7 | | |
| 2 | የደብዳቤ አፃፃፍ መመሪያ በመከተል የስራ/ማመልከቻና የግል ደብዳቤ መፃፍ | | | 2 | 3.7 |
| 3 | ቃላት በዐ.ነገር ውስጥ ያላቸውን አገባባዊ ና አውዳዊ ፍቺ መፃፍ | | | 2 | 3.7 |
| 4 | የተጋደሉ ሀሳቦችን አማልቶ መፃፍ | 3 | 11.11 | 1 | 1.9 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 5 | የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዩችን መርጦ አንቀጽ መፃፍ | 3 | 11.11 | 3 | 5.6 |
| 6 | ሰዋሰዋዊ ስህተት ያለባቸው ዐረፍተ ነገሮች አስተካክሎ እንደገና መፃፍ | 3 | 11.11 | 3 | 5.6 |
| 7 | ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ተግባራት ላይ ማስታወሻ ወስዶ መፃፍ | 2 | 7.4 | 2 | 3.7 |
| 8 | ስርአተ ነጥብ በተገቢው ቦታ መፃፍ | 2 | 7.4 | | |
| 9 | ግጥምመፃፍ | | | 3 | 5.6 |
| 10 | የህይወት ታሪክ መፃፍ | | | 3 | 5.6 |
| 11 | ቢጋር በማዘጋጀት አመዛዛኝናገላጭ/አስረጅ ድርሰት መፃፍ | | | 3 | 5.6 |
| 12 | የተሰጠው ሀሳብ በምሣሌው መሰረት በጹሁፍ አበራርቶ መግለፅ | 3 | 11.11 | 2 | 3.7 |
| 13 | የዐ.ነገሮች ስልትን መሰረት በማድረግ ዐ.ነገር መፃፍ | 1 | 3.7 | 1 | 1.9 |
| 14 | ግጥምን ወደ ዝርው ቀይሮ መፃፍ | | | 1 | 1.9 |
| 15 | አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት በዐ.ነገር ውስጥ አስተካክሎ መፃፍ | | | 1 | 1.9 |
| 16 | የዐ.ነገር ተዋቃሪ ክፍሎች ለይቶ መፃፍ | 3 | 11.11 | 1 | 1.9 |
| 17 | ምሣሌያዊ አነጋገሮች የሚያስተላልፉትን መልእክት መፃፍ | 2 | 7.4 | | |
| 18 | የድርሰት አፃፃፍመመሪያ በመከተል ድርሰት መፃፍ | 3 | 11.11 | 4 | 7.4 |
| 19 | በቃል ውስጥ የሚገኙት ስረወ ቃሎችና ቅጥያዎች ለይቶ መፃፍ | 1 | 3.7 | 1 | 1.9 |
| 20 | በዐ.ነገር ውስጥ ስማዊ ና ግሳዊ ሀረግ ለይቶ መፃፍ | | | 1 | 1.9 |
| 21 | በመረጡት ርዕሰ ጉዳይ አጭር ልቦለድ መፃፍ | | | 2 | 3.7 |

| | ድምር | 27 | 100% | 35 | 100% |
|---|---|---|---|---|---|

ከዚህ በላይ በቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከተለጣጣቂነት አንፃር በምን መልኩ እንደቀረቡ የምንመለከት ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፡- የተዘበራረቁ ዐ.ነግሮች ዕንደገና አስተካክሎ መፃፍ፣ስርአተ ነጥብ በተገቢው ቦታ ተጠቅሞ መፃፍ፣ምሣሌያዊ አነጋገሮች የሚያስተላልፉትን መልእክት መፃፍ፣ የሚሉት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡ ሲሆኑ በአስረኛ ክፍል ውስጥ አልተካተቱም፡፡

የደብዳቤ አፃፃፍ መመሪያ በመከተል የስራ /ማመልከቻና የግል ደብዳቤ መፃፍ፣ቃላት በዐ.ነገር ውስጥ ያላቸውን አገባባዊ እና አውዳዊ ፍቺ መፃፍ፣ግጥምመፃፍ፣የህይወት ታሪክ መፃፍ፣ ቢጋር በማዘጋጀት አመዛዛኝና ገላጭ /አስረጅ ድርሰት መፃፍ፣ ግጥምን ወደ ዝርው ቀይሮ መፃፍ፣አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት በዐ.ነገር ውስጥ አስተካክሎ መፃፍ፣በዐ.ነገር ውስጥ ስማዊ እና ግሳዊ ሀረግ ለይቶ መፃፍ፣በመረጡት ርዕሰ ጉዳይ አጭር ልቦለድ መፃፍ የሚባሉት የጽሕፈ ትክሂል ትምህርት ይዘቶች ደግሞ በአስረኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ ተካተው የቀረቡ ሲሆኑ በዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ አልተካተቱም፡፡

በአጠቃላይ የተለያዩ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተለጣጣቂነታቸውን ሳይጠብቁ በሁለቱ የክፍል ደረጃዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ቀርበው ይገኛሉ፡፡ ይህም በተተኳሪው መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችን ተለጣጣቂነት በሚመለከት ድክመት እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው፡፡

በመማሪያ መጻሕፍቶቹ ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተለጣጣቂነት በሚመለት የዘጠነኛ እና የአስረኛ ክፍል መጻሕፍት አዘጋጅ ከሆኑት ለአንዱ ‹‹እርሶ ባዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሐፍ ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ከተለጣጣቂነት አንፃር እንዴት ተደራጁ?›› በማለት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ‹‹ከተለጣጣቂነት አኳያ በአንዱ የክፍል ደረጃ ላይ ሙሉ በሙሉ በጥሩ ሁኔታ ሊዘጋጁ ይችላሉ፡፡ ይህም ማለት ከዘጠነኛ ወደ አስረኛ ክፍል ስንመጣ ግን እንደሚፈለገው ላይሄዱ ይችላሉ፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ክፍል በተለያዩ ባለሙያዎች የተሰሩ ስለሆኑ የሚተላለፉ ነገሮች ይኖራሉ የሚል እምነት አለኝ በማለት ሲገልፁ፤ ለምሳሌ ከፍ ባለው የክፍል ደረጃ /በ10ኛ ክፍል/ የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በዝቅተኛው የክፍል ደረጃ ከሚገኙት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በይዘቱም ሆነ በተግባሩ አነስ ያለ ሲሆን

የሚችልበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ነገር ግን ይህ እንዳይፈጠር ብዙ ጥረቶችን ለማድረግ ተሞክሯል፡፡ ቢሆንም ግን በይዘቶቹ ተለጣጣቂነት ላይ ክፍተት ይፈጠራል ብዬ አምናለሁ›› በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

በአስረኛ የክፍል ደረጃ በመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅነት ከተካተቱት ሁለት የመማሪያ መጽሐፉ አዘጋጆች መካከል በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም የአድራሻ ለውጥ በድማረግ እና በቦታ ርቀት ምክንያት ማግኘት ስላልተቻለ አንዳቸውንም በቃለ መጠይቁ ማሳተፍ አልተቻለም፡፡

ከዘነኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው ባዘጋጁት መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት የጽሕፈ ክሂል ትምህርት ይዘቶች ውስጥ ተለጣጣቂነት ትኩረት እንዳልተሰጠው ነው፡፡ ይህም በየክፍል ደረጃው ቀጣይነት ባለው መልኩ ተደራጅተው የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በየክፍል ደረጃው እያደጉ በሄዱ ቁጥር የይዘቶቹ ስፋትና ጥልቀት ወይም ከባድነት እንደዚሁም እያደጉ ወይም እየጨመሩ መሄድ እንደሚገባቸው ቀደም ሲል ተገልጧል፡፡ ይሁን እንጂ በዘጠነኛእና በአስረኛ ክፍል ባሉት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ተለጣጣቂነታቸውን ጠብቀው ከቀረቡት ዘጠኝ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ጥልቀታቸው እየጨመሩ ወይም የክብደት ደረጃቸው እያደጉ ተደራጅተዋል ወይስ አልተደራጁም የሚለውን ለማየት ምሳሌ ይሆነን ዘንድ የሚከተሉትን የዘጠነኛእና የአስረኛ ክፍል ባሉት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች እንመልከት፡፡

ተግባር፡-1. ከሀገራችን ከሚገኙት አራት ወቅቶች መካካል አንዱን መሰረት በማድረግ የወቅቶቹን ትክክለኛ ባህሪ የሚገልፅ መግቢያ፣ ሀተታ እና መደምደሚያ ያለው ድርሰት ፃፉ፡፡

(9ኛ ክፍል፣ ገፅ 56)

ተግባር፡-2. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ወይም በተለያየ መንገድ ስለተጽዕኖ ፈጣሪነታቸው ሲነገርላቸው የምትሰሟቸውን ጠንካራ አካል ጉዳተኛ ሰዎች አስመልክቶ መረጃ በመሰብሰብ ታሪካቸውን የሚገልፅ ድርሰት ፃፉ፡፡

(10ኛ ክፍል፣ ገፅ 77)

ከዚህ በላይ በዘጠነኛ እና በአስርኛ ክፍል ባሉት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በተለጣጣቂነት ከቀረቡት ዘጠኝ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተግባራት ማየት እንደሚቻለው በተሰጠ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ድርሰት መፃፍ ለማስተማር ታስቦ የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍ ውስጥ ልዩነት ባለው የአደረጃጀት ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ ቀርበው ይገኛሉ፡፡ የዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍል በተለጣጣቂነት

ቀርበው የሚገኙት እነዚህ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተግባራት ከክብደት አንፃር ሲታዩ አንድ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ስለ ድርሰት አፃፃፍ ህግጋት በማወቅ ማለትም ስለ መግቢያ፣ሀተታ እና መደምደሚያ የሚሉት ተግባራት በመከተል (በማጠናከር) ድርሰት እንዲፅፉ ያዛል፡፡ በመቀጠል ይህ ይዘት በአስረኛ ክፍል ውስጥም ጥልቀት አግኝቶ ተማሪዎቹ በአካባቢያቸው የምታውቋቸውን ወይም በተለያየ መንገድ ስለተጽዕኖ ፈጣሪነታቸው ሲነገርላቸው የምትሰሟቸውን ጠንካራ አካል ጉዳተኛ ሰዎች አስመልክቶ መረጃ በመሰብሰብ ታሪካቸውን የሚገልፅ ድርሰት እንዲፅፉ ያዛል፡፡ እነዚህም ተግባራት ከክፍል ክፍል ላቅ ብለውና ተለጣጣቂነታቸውን ከሞላ ጎደል ጠብቀው (ስፋትና ጥልቀት) አግኝተው የቀረቡ መሆናቸውን ከሰነድ ፍተሻው የተገኘው ውጤት ያሳያል፡፡

በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት ውጥ የቀረቡት ይዘቶች ስር ለጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተግባራት ከተለጣጣቂነት አንፃር በሰነድ ፍተሻው የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ይዘቶቹ ከክፍል ክፍል ተከታታይ በመሆን ጥልቀት እያገኙና ትምህርቱ እየጎለበተ የሚሄድበት የአደረጃጀት ስልት መሆኑን በምዕራፍ ሁለት ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡

ከሰንጠረዥ ዘጠኝ መገንዘብ እንደሚቻለው የዘጠነኛ እና የአስርኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በአጠቃላይ 21 የተለያዩ አይነት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ይገኛሉ፡፡ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ከተካተቱት አጠቃላይ ይዘቶች መካከል ዘጠኞቹ (16.7%) ያህልቹን በተተኳሪዎቹ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ ያለምንም መቆራረጥ ተለጣጥቀው ቀርበዋል፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ ከአጠቃላዩ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች መካከል 12 (83.3%) ያህሉቹ የተለያዩ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በተተኳሪዎቹ የክፍል ደረጃዎች መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ተለጣጥቀው የመቅረብ ችግር /ድክመት/ እንዳለባቸው ያሳያሉ፡፡

በአጠቃላይ በዘጠነኛ እና በአስርኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተለጣጣቂነት ለማየት በተደረገው ጥረት ከሁለቱም የመረጃ ምንጮች የተገኘው ውጤት እንደሚያረጋግጡት በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በተለጣጣቂነት የመቅረብ ድክመት ይታይባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡረት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ሙሉ በሙሉ ተለጣጣቂነት የላቸውም ማለት ግን አይደለም፡፡

### 4.3.3 የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት አንፃር

በክለሳ ድርሳን ለመግለፅ እንደተሞከረው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ስልት ለተማሪዎች ምንም አይነት ገለፃ /ማብራሪያ ሳይሰጣቸው የቀረበላቸውን ምሳሌዎች በመመርኮዝ የታላሚን ቋንቋ ስርአት ወይም ህግጋት እንዲያቁና እንዲለማመዱ የሚያግዝ ስልት ነው፡፡ በዚህ ስልት ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን በማለማመድና በሂደት የታላሚን ቋንቋ ስርአት ወይም ህግጋት ያውቁታል፡፡ በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት ሁለቱም በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ይህንን የአደረጃጀት ስልት ተከትለው የቀረቡ መሆናችውን በተደረገው ፍተሻ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ቀጥሎ እያንዳንዱ የክፍል ደረጃ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አስረጂዎችን በመውሰድ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

**ሀ. የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ**

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በቅድሚያ የታላሚውን ቋንቋ የመፃፍ ስርአት ወይም ህግጋት የሚያሳዩ ምሳሌዎችን በማቅረብ ተማሪዎች በሂደት ህግጋቱን ለይተው እንዲያውቋቸው የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ ስለዚህም ተማሪዎቹ ምሳሌዎቹን ተከትለው የቀረቡ ጥያቄዎቹን በመስራት ህግጋቱን በሂደት ይለምዷቸዋል ማለት ነው፡፡ ይህም የመማሪያ መጽሐፉ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአደረጃጀት ስልትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች እንደቀረቡ ያሳያል፡፡ የሚከተሉትን በምሳሌነት እንመልከት፡-

ተግባር፡-1. ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ተዋቃሪ ሆነው የሚገኙትን የስም ገላጮችና ተገላጭ ስሞች ለይታችሁ ፃፉ፡፡

ምሳሌ፡-ሀ. ኢትዮጵያ ትልቅ ግድብ እየገነባች ነው፡፡

የስም ገላጭ፡- ትልቅ

ተገላጭ ስም፡- ግድብ

ሀ. ተማሪዋ ረጅም ቀሚስ መልበስ ትወዳለች ፡፡

ለ. ቱሉ አዲስ መኪና ገዛ፡፡

ሐ. ጫት መቃም ጎጂ ልማድ ነው፡፡

መ. ግመል የሚኖረው በረሀማ አካባቢ ነው፡፡

(9ኛ ክፍል፣ገፅ- 8)

ከቀረበው ምሳሌ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች ምሳሌውን በማጤን ወይም በመከተል የቀረቡትን በአረፍተ ነገር ውስጥ ተዋቃሪ ሆነው የሚገኙትን የስም ገላጭና ተገላጭ ስም

ለይተው ይጽፋሉ። ተግባራቱ ወይም ጥያቄዎቹን በመስራት በሂደት በአረፍተ ነገር ውስጥ ተዋቃሪ ሆነው የሚገኙትን የስም ገላጭና ተገላጭ ስም ይለያሉ። ከእነዚህም ተግባራቶች ወይም ጥያቄዎች በፊት ምንም አይነት ማብራሪያ /ገለፃ የለም። ይህም በተተኳሪው የክፍል ደረጃ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአደረጃጀት ስልት ተከትለው የቀረቡ መሆኑን ከሰነድ ምልከታው መረጋገጡን ያሳያል።

ተግባር፡-2. ቀጥሎ ከምንባቡ የተወሰዱ ሀረጎችና ዐ.ነገሮች ቀርበዋል። በእነዚህ ሀረጎችና ዐ.ነገሮች ውስጥ የምታዩአቸውን ሰዋሰዋዊ ስህተቶች፤ በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ትክክለኛ ቅርፅ በመፈለግ እንደገና አስተካክላችሁ ጻፉ።

ምሳሌ፡- በበሽታው ተይዣለሁ እንጂ ነፃ ነኝ። (ይህ ስህተት ያለበት ዐ.ነገር ነው።)

ስህተቱ የተፈጠረው እንጂ የሚለው አያያዥ ቃል ያለ ቦታው በመግባቱ ነው።

በበሽታው ተይዣለሁ ወይስ ነፃ ነኝ? (ተስተካክሎ የተፃፈ ዐ.ነገር ነው)

1. ለመቆጣጠር በጣም አዳጋች የሆነ ህመሞች ናቸው።
2. የሰው ልጅ በመላው አለም እተስፋፉ ሄዱ።
3. ተላላፊ የሆኑ በሽታዎች በዛው ልክ ሊስፋፋ ችለዋል።
4. የአለም ህዝብ ራስ ምታት ለመሆን በቅቶታል።

(9ኛ ክፍል፣ገፅ -38)

ከላይ በምሳሌነት የቀረቡትን አሰረጂዎች በምንመለከትበት ወቅት ተማሪዎች በተግራቱ ውስጥ የቀረቡትን አረፍተ ነገሮችና ሀረጎች ውስጥ የምታዩአቸውን ሰዋሰዋዊ ስህቶች በተሰጣቸው ምሳሌ፤ በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ትክክለኛ ቅርፅ በመፈለግ እንደገና አስተካክለው እንዲፅፉ ያዛል። ይህም በዚህ መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ መልኩ /ስልት ተደራጅተው መቅረባቸው ያሳየናል። ከሰነድ ፍተሻው ማረጋገጥ እንደተቻለው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂልት ምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ተከትለው የቀረቡ ናቸው። በዚህም የክፍል ደረጃ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት የቀረቡት ይዘቶች ከአስረኛ ክፍል መፃህፍት አኳያ በተሻለ ሁኔታ የቀረቡ መሆናቸውን ከሰነድ ምርመራውን ማረጋገጥ ተችሏል ።በዚህ በዘጠነኛ የክፍል ደረጃ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ከሆኑት ውስጥ ለአንዱ ‹‹እርሶ ባዘጋጁት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ከአደረጃጀት መስፈርቶች አንፃር እንዴት ተደራጁ? ለምሳሌ

ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አንፃር?›› በማለት ቀለረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ‹‹በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተግባራት ተማሪው በራሱ እንዲሰራ የሚያደርጉ ምሳሌዎች ያሏቸው ናቸው። ተማሪዎች የቋንቋውን ህግጋት እራሳቸው በሂደት እንዲያውቁት በሚያስችላቸው መልኩ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ተደራጅተው ቀርበዋል›› የሚል ነው። በአጠቃላይ ከሁለቱም የመረጃ ምንጮች ማለትም ከሰነድ ፍተሻውና ከቃለ መጠየቁ ማረጋገጥ እንደተቻለው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተካተው የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተግባራት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ስልትን ተከትለው የቀረቡ መሆናቸውን ነው።

**ለ. የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ**

በአስረኛው የክፍል ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በቅድሚያ የታላሚውን ቋንቋ የጽሕፈት ስርአት ወይም ህግጋት የሚያሳዩ ምሳሌዎችን በማቅረብ ተማሪዎች በሂደት ህግጋቱን ለይተው እንዲያውቋቸው የሚያበረታቱ ናቸው። ስለዚህም ተማሪዎቹ ምሳሌዎቹን ተከትለው የቀረቡ ጥያቄዎቹን በመስራት ህግጋቱን በሂደት ይለምዷቸዋል ማለት ነው። ይህም የመማሪያ መጽሐፍ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአደረጃጀት ስልትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች እንደቀረቡ ያሳያል። የሚከተሉትን በምሳሌነት እንመልከት።

ተግባር፡-1. ቀጥሎ በቀረቡት ጽሑፎች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት በሚገኙበት አውድ መሰረት ያላቸውን አገባባዊ ፍች ጻፉ።

1 .ለረጅም ጊዜ በሱስ መጠመድና ተጋላጭ መሆን ያእምሮ ጉዳት፣የማስታወስ ክህሎት ማሽቆልቆል፣

ተስፋመቁረጥ፣እራስን መቆጣጠር አለመቻልና ሌሎች ተጓዳኝ የአካልና የስነ-ልቦና ቀውሶችንና ሞትንሊያስከትል ይችላል።

2. ጓደኛ ጎንበስ ብሎ ወደ ውስጥ ሲጋ፣ሹራቡ ወደ ላይ ተሳና ጀርባው ኩል የወሸቃቸውን ድተሮች አጋለጣቸው።

3. ድሀው ከባርነቱ አረንቋ አወጣች።

4. ምን አልባት የሀገርና የህዝብ ክብርና ኩራት፣ህላዌና ፈቃድ ጠባቂ፣ አስከባሪና ባላደራ ስለሆነ ይሆናል።

5. በእቅድ መስራት አይሆንልንም። ያዘው ጥለፈው ማለት ነው የሚቀናን። እውነቱን ነው … እስኪ የልደታችንን፣ የሰርጋችንን፣ የሞታችንን፣ የኑሯችንንና የአመጋገባችንን ሁኔታ አስበው።

ግብታዊነት ይበዛበታል፡፡ በግብታዊ አሰራር እንደእኛ አይነት ህዝብ በዓለም ላይ ያለ አይመስለኝም፡፡

(10ኛ ክፍል፣ ገፅ - 37)

ከላይ በምሳሌነት የቀረቡትን አሰረጂዎች በምንመለከትበት ወቅት ተማሪዎች በተግራቱ ውስጥ የቀረቡላቸውን ምሳሌዎችን በመመርኮዝ /በማስተዋል የቀረቡትን ቃላት በዐ.ነገር ውስጥ ያላቸው አገባባዊ ፍቺ ይፅፋሉ፡፡ ተግባራቱ ወይም ጥያቄዎቹን በመስራት በሂደት የቃላት አገባባዊ ፍቺ በዐ.ነገሮቹ ውስጥ ያላቸውን ትርጉም ይለያሉ፡፡ ከእነዚህም ተግባራቶች ወይም ጥያቄዎች በፊት ምንም አይነት ማብራሪያ/ገለፃ የለም፡፡ ይህም በዚህ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ መልኩ/ ስልት ተደራጅተው መቅረባቸው ያሳየናል፡፡ ከሰነድ ፍተሻው ማረጋገጥ እንደተቻለው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት ተከትለው የቀረቡ ናቸው፡፡ በዚህም የክፍል ደረጃ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት የቀረቡት ይዘቶች ከሌሎቹ ተተኳሪ መፃህፍት አኳያ በተሻለ ሁኔታ የቀረቡ መሆናቸውን ከሰነድ ምርመራውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በዚህ የክፍል ደረጃ በመማሪያ መጽሐፉ አዘጋጅነት ከተካተቱት ሁለት የመማሪያ መጽሐፉ አዘጋጆች መካከል በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም የአድራሻ ለውጥ በድማረግ እና በቦታ ርቀት ማግኘት ስላልተቻለ አንዳቸውንም በቃለ መጠይቁ ማሳተፍ አልተቻለም፡፡

### 4.3.4 የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት አንፃር

ከላይ በክለሳ ድርሳን ለመግለፅ እንደተሞከረው የዚህ የአደረጃጀት ስልት በቅድሚያ የታላሚውን ቋንቋ የጽሕፈት ስርአት ወይም ህግጋት የሚያሳዩ ማብራሪያችንና ገለፃዎችን ለተማሪዎች ይቀርብላቸዋል፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች በገለፃ መልክ የቀረበላቸውን ህግጋት ወይም ስርአት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ለመለማመድ ይረዳል፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢም በተተኳሪዎቹ የክፍል ደረጃ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ስልት በመፈተሽ በሁለቱንም የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በዚህ ስልት ተደራጅተው የቀረቡ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች መኖራቸውን አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ከዚህ ቀጥሎ በየክፍል ደረጃው በአስረጅነት የቀረበውን እንመልከት፡፡

ሰንጠረዥ 8. በተተኳሪዎቹ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ የጽሕፈት ክሂል ምህርት ይዘቶች ማብራሪያዎች፣ ብዛት፣ አይነትና መገኛ ገፅ

| ተ/ቁ | በቋንቋ በመማሪ መፃህፍቶች ውስጥ የሚገኙ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ማብራሪያዎች ዝርዝር ይዘቶች | የክፍል ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | 9ኛክፍል | | 10ኛክፍል | |
| | | ብዛት | መገኛ ገፅ | ብዛት | መገኛ ገፅ |
| 1 | ሰዋሰዋዊ ስህተት ያለባቸው ዐረፍተ ነገሮች አስተካክሎ እንደገና መፃፍ | 3 | 38፣39፣48 | 3 | 38፣79 |
| 2 | በቃል ውስጥ የሚገኙት ስረወ ቃሎችና ቅጥያዎች ለይቶ መፃፍ | 1 | 91 | 1 | 91 |
| 3 | ቃላት በዐ.ነገር ውስጥ ያላቸውን አገባባዊ ና አውዳዊ ፍቺ መፃፍ | | | 2 | 37፣58 |
| 4 | ግጥምን ወደ ዝርው ቀይሮ መፃፍ | | | 1 | 89 |
| 5 | የተጓደሉ ሀሳቦችን አማልቶ መፃፍ | 6 | 2፣6፣26፣27፣33፣43 | 1 | 87 |
| 6 | የዐ.ነገር ተዋቃሪ ክፍሎች ለይቶ መፃፍ | 4 | 8፣28፣49፣101 | 1 | 106 |
| 7 | ምሣሌያዊ አነጋገሮች የሚያስተላልፉትን መልእክት መፃፍ | 2 | 16፣19 | | |
| 8 | የተዘበራረቁ ዐ.ነግሮች ዕንደገና አስተካክሎ መፃፍ | 3 | 38፣68፣89 | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 9 | የዐ.ነገሮች ስልትን መሰረት በማድረግ ዐ.ነገር መፃፍ | 1 | 13 | 1 | 106 |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው በዘጠነኛ እና በአስረኛ (9ኛ-10ኛ) ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት የተካተቱት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተግባራት ብዛትና መገኛ ገጾች ተለይተው ቀርበዋል፡፡ እነዚህንም ተግባራት ማብራሪያዎች ቀጥሎ በየክፍል ደረጃው እንመለከታለን፡፡

**ሀ. የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ**

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሰባት ልዩ ልዩ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ማብራሪያዎች /ገለፃዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህም ሰዋሰዋዊ ስህተት ያለባቸው አረፍተ ነገሮች አስተካክሎ እንደገና መፃፍ (ገፅ፤38፣39፣48)፤ በቃል ውስጥ የሚገኙት ስረወ ቃሎችና ቅጥያዎች ለይቶ መፃፍ (ገፅ፤97)፣ የተጓደሉ ሀሳቦችን አማልቶ መፃፍ (ገፅ፤2፣6፣26)፣ የዐ.ነገር ተዋቃሪ ክፍሎች ለይቶ መፃፍ (ገፅ፤8፣28፣49፣)፣ምሣሌያዊ አነጋገሮች የሚያስተላልፉትን መልእክት መፃፍ (ገፅ፤16)፣የተዘበራረቁ ዐ.ነግሮች ዕንደገና አስተካክሎ መፃፍ፣መፃፍ (ገፅ፤89) እና የዐ.ነገሮች ስልትን መሰረት በማድረግ ዐ.ነገር መፃፍ (ገፅ፣13) የሚለት ማብራሪያዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ ልዩ ልዩ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ማብራሪያዎች /ገለፃዎች አስቀድመው ስለ ርዕሰ ጉዳያቸው ገለፃ ካደረጉ በኃላ ምሳሌዎችን ያሳያሉ፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች የሚለማመደባቸው ልዩ ልዩ ተግባራት ያቀርባሉ፡፡ ይህም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተግባራት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአደረጃጀት ስልት መደራጀታቸውን ያሳያሉ፡፡ የሚከተለውን አንድ አስረጅ በመውሰድ እንመልከት፡፡

# የዘገባ አጻጻፍ መመሪያ

ዘገባ አዘጋጅታችሁ በምታቀርቡበት ጊዜ ለሚከተሉት ጉዳዮች ትኩረት አድርጉ፡፡

*1. ለዘገባችሁ ያሰባሰባችኋቸውን መረጃዎች በማመዛዘንና በማነጻጸር ሥርኣት ባለው መንገድ ተንትናችሁ ሀሳቡ ግልጽ እንዲሆንላችሁ አድርጉ፡፡ ዘገባውን ከመጻፋችሁ በፊት አስተዋጽኦ አዘጋጁ፡፡*

2. መረጃዎቻችሁን መነሻ በማድረግ በነደፋችሁት አስተዋጽኦ መሰረት የዘገባውን ዋና አካል ጻፉ፡፡

3. በዘገባው ውስጥ ተደጋጋሚ እርስበርስስ የሚቃረኑ ሀሳቦች እንዳይኖሩ ጥንቃቄ አድርጉ፡፡

4. ዘገባውን ቀላልና ግልጽ በሆነና በማያሰለች ቋንቋ ጻፉ፡፡

*5. መረጃዎቻችሁን ስታሰባስቡ ያጋጠሟችሁን ችግሮችና የተጠቀማችሁባቸውን መፍትሄዎች የሚጠቁም መግቢያ በመጨረሻም አጠር ያለ ማጠቃለያ ጻፉ፡፡*

6. በዘገባ ጽሁፉ የመጀመሪያ ገጽ መሀል ላይ የዘገባውን ርእስ ጻፉ፡፡

*7. በዚሁ ገጽ ላይ ከርእሱ ስር የዘጋቢውን/ዘጋቢዎችን ሥም ጻፉ፡፡*

*8. በዚሁ ገጽ የቀኝ ግርጌ ዘገባው የተጻፈበትን ቀንና ቦታ ጻፉ፡፡*

*፩.* በሀገራችን ከኮሮና በሽታ መከሰት ጋር ችግሮተያይዞ በርካታ ችን ማለፋችን ይታወቃል፡፡ በኮሮና ምክንያት ትምህርት ቤቶች ተዘግተው ነበር፤ ቤት እንድንቀመጥ ተደርገን ነበር፣ በትራንስፖርት አጠቃቀም ላይ ህግ ወጥቶ ነበር፤ ወዘተ፡፡ እናንተም የኮሮና ወረርሽኝ በተከሰተበት ወቅት ምን ተሰምቷችሁ እንደነበር፣ በአካባቢያችሁ በወቅቱ ምን ምን ሲደረግ እንደ ነበር፣ ባጠቃላይ ያንን የውጥረት ጊዜ እንዴት እንዳሳለፋችሁት፣ ወዘተ. በመግለፅ ዘገባ ጽፋችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡ ዘገባውን መፃፍ ከመጀመራችሁ በፊት ከላይ የቀረበውን የዘገባ አፃፃፍ መመሪያ ተመልከቱ፡፡

*(9ኛ ክፍል፣ገፅ- 37)*

ከቀረበው አስረጅ መገንዘብ እንደሚቻለው በቅድሚያ ለተማሪዎች ስለ ዘገባ አፃፃፍ መመሪያ እንዲገነዘቡ ቀርቦሏቸዋል፡፡ ከእነዚህም ማብራሪያዎች በኂላ ተማሪዎች በቀረበላቸው ልዩ ልዩ ተግባራት ውስጥ እየተለማመዱ ይቆዩና ከማብራሪያዎች ያገኙትን ተጨባጭ ነገር ተግባራዊ እያደረጉ ይሄዳሉ ማለት ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቱ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአደረጃጀት ስልት መርህ ተከትሎ ቀርበዋል ለማለት አይስደፍርም ፡፡ ምክንያቱም በዚህ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የፅሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአደረጃጀት ስልት የተደራጁ መሆኑን በተደረገው ጥረት ከሰነድ ምርመራው በተገኘው ውጤት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚሁ የክፍል ደረጃ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው አንደ የመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ‹‹እርሶ ባዘጋጁት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጸሐፍ ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ከአደረጃጀት መስፈርቶች አንፃር እንዴት ተደራጁ? ለምሳሌ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አንፃር?›› በማለት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ‹‹ይዘቶች በሚደራጁበት ጊዜ እነዚህ ይዘቶች አዳዲስ ፅንሰ ሀሳቦች ሲኖራቸው ለተማሪዎች አንዳንድ ማብራሪያዎችን ቀርበዋል፡፡ ምንም እንኳን በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአደረጃጀት ስልት ተከትለው የቀረቡ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ቢኖሩም በበቂ ሁኔታ የቀረቡ ናቸው ለማለት እንደማያስደፍር ነው፡፡

**ለ. የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ**

በዚህ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ደግሞ ሰባት የተለያዩ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ገለፃዎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህም ሰዋሰዋዊ ስህተት ያለባቸው ዐረፍተ ነገሮች አስተካክሎ እንደገና መፃፍ (ገፅ፤38፣79)፣ በቃል ውስጥ የሚገኙት ስረወ ቃሎችና ቅጥያዎች ለይቶ መፃፍ (ገፅ፣ 91) ቃላት በዐ.ነገር ውስጥ ያላቸውን አገባባዊ እና አውዳዊ ፍቺ መፃፍ (ገፅ፣37፣58) ግጥምን ወደ ዝርው ቀይሮ መፃፍ (ገፅ፣89)፣ የተጓደሉ ሀሳቦችን አማልቶ መፃፍ (ገፅ፣87) የዐ.ነገር ተዋቃሪ ክፍሎች ለይቶ መፃፍ (ገፅ፣106) የዐ.ነገሮች ስልትን መሰረት በማድረግ ዐ.ነገር መፃፍ (ገፅ፣106) የሚሉት ናቸው፡፡ እስኪ በምሳሌነት አንዱን ተግባር ወስደን እንመልከት፡፡

<u>የአረፍተ ነገር አወቃር</u>

አረፍተ ነገር የሚዋቀረው ከሁለት ነገሮች ነው፡፡ እነዚህም ስማዊና ግሳዊ ሀረጎች ናቸው፡፡

ምሳሌ፡- ያ ትልቅ ልጅ አንድ የሰዋስው ደብተር ገዝቷል፡፡

ከላይ በምሳሌነት የተሰጠው አረፍተ ነገር የጠዋቀረው፣

ሀ. ያ ትልቅ ልጅ

ለ. አንድ የሰዋስው ደብተር ገዝቷል፡፡ ከሚሉት ሁለት ሀረጎች ነው፡፡ የመጀመሪያው ሀረግ ስማዊ ሲሆን፣ ሁለተኛው ግሳዊ ነው፡፡

ይህ ስለ ሰዋስው ደብተር መግዛት ተግባር የተነገረ አረፍተ ነገር ነው፡፡ ገዥው ሰው ማን እንደሆነ፣ የተገዛው ነገር ምን እንደሆነ ተገልፆል፡፡ በሌላ አነጋገር አረፍተ ነገሩ ሙሉ ሀሳብን ይገልፃል፡፡ ስለዚህም ተናጋሪው ሌላ ሀሳብ እስኪመጣለት ድረስ ሊያርፍ ይችላል፡፡ እንደዚ ያለ የተሟላ ሀሳብ የሚገልፅ መዋቅር አረፍተ ነገር ይባላል፡፡

(10ኛ ክፍል፣ ገፅ- 48)

ተግባር 1. ከዚህ በታች  የሚገኙት አረፍተ ነገሮች ሰዋስዋዊ ስህተቶች ያሉ ባቸው ስለሆኑ አስተካክላችሁ ጻፏቸው፡፡

1. አለማየሁና በላይ ከትምህርት ቤት መጣ፡፡

2. አበበ ጎበዝ ተማሪ ናቸው፡፡

3. እኔ ደግሞ ወደ ትምህርት ቤት መሄድ የምፈልገው ከነደበላ ጋር ነኝ፡፡

4. እኔ አንተን እወድሻለሁ፡፡ ከበደም አንተን ትወዳለች፡፡

ከላይ በአስረጅነት የቀረበው የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘት በምንመለከትበት ወቅት አስቀድሞ ስለ ዐ.ነገር  ተዋቃሪ ክፍሎች/ ስለ አረፍተ ነገር አወቃቀር ምንነት ገለጻ ከሰጠ በኃላ ማብራሪያዎቹን /ገለፃዎቹን መሰረት ያደረጉ ተግባራት በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ቀርበዋል፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ በመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅነት ከተካተቱት ሁለት የመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች መካከል በተለያዩ ምክንያቶች ማለትም የአድራሻ ለውጥ  በማድረግ እና በቦታ ርቀት ማግኘት ስላልተቻለ አንዳቸውንም በቃለ መጠይቁ ማሳተፍ አልተቻለም፡፡

## 4.4 የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ትኩረት የ9ኛእና የ10ኛ የክፍል ደረጃዎች መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ንፅፅራዊ ግምገማ ነው፡፡ በመሆኑም በሰነድ ፍተሻ እና በቃለ መጠይቅ በተሰበሰቡት መረጃዎች የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጀጀት የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ምን ምን አይነት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች እንደተካተቱ መለየት፣የ9ኛእና የ10ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችን አደረጃጀት ከአደረጃጀት መስፈርቶች አንፃር መደራጀታቸው ፈተሾ መገምገም እና የ9ኛእና 10ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት

ክሂል ምህርት ይዘቶችና የአደረጃጀታቸውን ምላተ ቀርነታቸውን በንፅፅር መገምገምና ከውጤቱ በመነሳት አስታየት መሰንዘር የሚሉት ለመፈተሽ መረጃዎች በገላጭ የምርምር ስልት ተተንትነዋል፡፡

በጥናቱ ውጤት ትንተና በቅድሚያ ምላሽ የተሰጠው ጉዳይ የ9ኛእና 10ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ምን ምን አይነት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች እንደተካተቱ መለየትን የሚመለከት ነው፡፡ በጥናቱ ውጤት መሰረት በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አይነቶች ዝርዝር ስንመለከት ለምሳሌ በተሰጠው ርዕሰ ጉዳይ ስር ተዘበራርቀው የቀረቡ አረፍተ ነገሮችን እንደገና አስተካክሎ መፃፍ፤ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን መርጦ አንቀፅ መፃፍ፤የተጓደሉ ሀሳቦችን አሟልቶ መፃፍ፤ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ ያላቸውን አገባባዊና አውዳዊ ፍቺ መፃፍ፤የደብዳቤ አፃፃፍ መመሪያ መሰረት በማድረግ የስራ/ የማመልከቻና የግል ደብዳቤ መፃፍ፤ግጥም መፃፍ ወዘተ የሚለትን መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል፡፡

ከጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች አንፃር በውጤት ትንተና ላይ ሌላኛው ትኩረት የተደረገበት ጉዳይ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ከአደረጃጀት መስፈርቶች አንፃር መደራጀታቸው ፈተሾ መገምገም ነው፡፡ ይህም በሰንጠረዥ 5፣6፣7 እና 8 እንደየክፍል ደረጃ ቅደም ተከተል በሁለቱም የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በ9ኛ ክፍል 11.5%፣በ10ኛ ክፍል 4.9% የሚደርሱ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አንዴ ብቻ ቀርበው ተከታታይነታቸው ሳይደጋገሙ የቀሩ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በቃለ መጠይቅ በተገኘው ውጤት መሠረት የመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች የ9ኛእና የ10ኛ የክፍል ደረጃ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ከምዕራፍ ምዕራፎች ሆነ ከክፍል ክፍል ያላቸውን ተከታታይነት ሙሉ በሙሉ አላቸው ብሎ መናገር የሚያስደፍር አይደለም ብለዋል፡፡

በመሆኑም እነዚህ ጥቂት የሚሆኑ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተከታታይነት እንደሌላቸው ያመለከተው የዚህ ጥናት ውጤት ከCunningsworth (1995)፣ Freeman (1991) እና ተስፋዬ (1981) በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ እያንዳንዱን የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ተደጋግመው መምጣት አለባቸው፡፡ ነገር ግን እንደ አዲስ የቋንቋ ትምህርት ይዘት አንድ ጊዜ ብቻ መቅረቡ በቂ ነው ፡፡ በማለት ከደረሱበት የድምዳሜ ንድፈ ሀሳብ ጋር የተለያየ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ በጥናቱ ውጤት መሰረት በሁለቱም የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በ9ኛ ክፍል 88.5%፣ በ10ኛ ክፍል 95.1 % ተከታታይነታቸውን ጠብቀውና ስፋት ጥልቀታቸውን እየጨመሩ እየሄዱ መሆናቸውን የዚህ ጥናት ውጤት አመላክቷል፡፡ ይህም ውጤት ከCunningsworth(1995)፣ Freeman(1991) እና ተስፋዬ (1981) ካቀረቡት የጥናት ውጤት ድምዳሜ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም ከCunningsworth(1995)፣ Nunan(1988)እና Yelden(1987) ተዋረዳዊ ግንኙነት በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚኖረውን የይዘት አደረጃጀትና ቅደም ተከልን የሚያመለክት ከመሆኑም በተጨማሪ ቀደም ሲል በተማሩትና በሚቀጥለው የክፍል ደረጃ በሚማሩት የይዘት አደረጃጀት ላይ መያያዝ ይኖርበታል ከሚለው ንድፈ ሐሳብ ጋር ይደጋገፋል፡፡

በሌላ መልኩ በሁለቱም በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ከተደራጁት 21 የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች 12 ቶዎቹ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተለጣጣቂነታቸውን ያልጠበቁ ወይም የመቆራረጥ ችግር ያለባቸው መሆናቸውን የዚህ ጥናት ውጤት አመላክቷል ፡፡ ይህም ውጤት ከFreeman(1991)፣ Nunan(1988)እና Yelden(1987) ተለጣጣቂነት በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የትምህርቱን ይዘቶች ቀጣይነት ባለው መልኩ ሳይቆራረጡ እርስ በእርስ ተሳስረው መደራጀት እንዳለባቸውና ተለጣጣቂነታቸው ወይም ቀጣይነታቸው ከክፍል ወደ ክፍል እያደጉና ጥልቀታቸውም እየጨመሩ የሚሄዱ መሆን ይኖርባቸዋል በማለት ካቀረቡት ንድፈ ሀሳብ ጋር ይቃረናል፡፡ (9) ዘጠኙ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ብቻ ሳይቆራረጡ ከደረጃ ደረጃ ወይም ከክፍል ክፍል ስፋትና ጥልቀታቸው ጠብቀው እንዲቀረቡና ተለጣጣቂነት እንዳላቸው የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡ ይህም ከFreeman(1991)፣ Nunan (1988) እና Yelden(1987) የንድፈ ሀሳብ ውጤት ጋር ይመሳሰላል፡፡

በተጨማሪም በዚህ ጥናት በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ከቀረቡት 21 የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች 12 ቶዎቹ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተለጣጣቂነታቸውን ያልጠበቁ ወይም የመቆራረጥ ችግር ያለባቸው ናቸው ያለው የዚህ ጥናት ውጤት ከፅጌ (1992) እና ተሻለ (2005) በጥናታቸው የደረሱበት ማጠቃለያ በሁለቱም ክፍሎች የፅህፈት ክሂል ይዘቶችን የቀረበውን የተለጣጣቂነት መስፈርት በአግባቡ ስራ ላይ አለመዋሉንና ለዚህም አብይ ምክንያት የሆነው ይዘቶቹ የተማሪዎችን ችሎታ የሚመጥኑ ሆነው ያለመመረጣቸው ናቸው በማለት ከደረሱበት የጥናት ውጤት ጋር ይመሳሰላል፡፡

በጥናቱ ሌላኛው ትኩረት የተደረገበት ጉዳይ የ9ኛእና የ10ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችና የአደረጃጀታቸውን ምላተ ቀርነት ገምግሞ በመለየት ከውጤቱ በመነሳት አስታየት መሰንዘር የሚመለከት ነው፡፡ ከላይ በሰንጠረዥ 3 ስር በጥናቱ ውጤት ትንተና እንደቀረቡት በሁለቱም መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ያሉትና የሌሉትን የዚህ ጥናት ውጤት አረጋግጧል፡፡

በአጠቃላይ በክለሳ ድርሳን ክፍል እንደቀረበው Cunningsworth(1995)፣Nunan(1988)እና Yelden(1987) ተዋረዳዊ ግንኙነት በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚኖረውን የይዘት አደረጃጀትና ቅደም ተከትልን የሚያመለክት ከመሆኑም በተጨማሪ ቀደም ሲል በተማሩትና በሚቀጥለው የክፍል ደረጃ በሚማሩት የይዘት አደረጃጀት ላይ መያያዝ ይኖርባቸዋል የሚሉ የንድፈ ሀሳብ ውጤቶች አመላክቷል፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ውጤትም በሁለቱ መማሪያ መፃሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በሚፈለገው ልክ አልተደራጁም ወደሚል መደምደሚያ ያደረሳል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፤ማጠቃለያ ፣ መደምደሚያ እና የመፍትሔ ሀሳብ

## 5.1 ማጠቃለያ

በምዕራፍ አንድ እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአዲሱ የ9ኛእና የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሐፍት ውስጥ የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት በንፅፅር መገምገም እንደሆነ ተገልጸዋል፡፡ ይህ ምዕራፍ ደግሞ በሰነድ ምርመራና በቃለ መጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰቡ መረጃዎች ውጤት የሚተነተኑበት ነው፡፡ በዚህ መሰረት ይህ ጥናት ይመልሳቸዋል ተብለው የቀረቡት ዝርዝር አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ/ በ9ኛእና በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ተርመርጠው የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት መፈተሽ፣

ለ/ በ9ኛእና 10ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችን አደረጃጀት ከአደረጃጀት መስፈርቶች አንፃር መገምገም፣

ሐ/ በ9ኛእና በ10ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችና የአደረጃጀታቸውን ምላተ ቀርነታቸውን በንፅፅር መፈተሽ ናቸው፡፡

የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ለተማሪውም ሆነ ለመምህሩ ብሎም ለመማር ማስተማሩ ክንውን ቁልፍ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ መጻሕፍቱ የሚፈለግባቸውን ድርሻ መወጣት ይችሉ ዘንድ ሁለንም የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች አመጣጥነው መያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ውስጥ ደግሞ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘት አንዱ ነው፡፡ ስለዚህ በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ከተካከቱት ይዘቶች ውስጥ የጽሕፈት ክሂልም የተወሰነ ድርሻ እንዲኖረው ይጠበቃል፡፡ ይህ በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የራሱ ድርሻ ተሰጥቶት ከሌሎች የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በተጓዳኝ የሚቀርበው የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችም የደረጃ መሰፈርቶች መሰረት በማድረግ በይዘቶቹ መካከል መኖር የሚገባውን ተከታታይነት፣ ተለጣጣቂነት፣ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የአደረጃጀት መርሆችን መነሻ በማድረግ በ9ኛእና10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ላይ በተደረገው ግምገማ መሰረት ይዘቶች ፡-

- ✓ በሁለቱም የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በ9ኛ ክፍል ከ12ቱ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ውስጥ 88.5%፣ በ10ኛ ክፍል ከ17ቱ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ውስጥ 95.1%

ተከታታይነታቸውን ጠብቀውና ስፋት ጥልቀታቸውን እየጨመሩ የመሄድ ሁኔታዎች መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ታይቶባቸዋል፡፡ ነገር ግን በሁለቱም የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በ9ኛ ክፍል 11.5%፣ በ10ኛ ክፍል 4.9% የሚደርሱ የፅሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አንዴ ብቻ ቀርበው ሳይደጋገሙ የቀሩ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች መኖራቸውን ለማየት ተችሏል ፡፡ይህም በእነዚህ መማሪያ መጻሕፍት የተካተቱት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከተከታታይነት አንፃር ክፍተት የሚታይባቸው መሆኑን ይጠቁማል፡፡

- ✓ በሁለቱም ክፍሎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት ጥቂት የሚሆኑ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከአጠቃላይወደ ዝርዝርእና ከዝርዝርወደ አጠቃላይ የአደረጃጀት ስልት ተደራጅተው ይገኛሉ፡፡ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የአደረጃጀት ስልት በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት ከፍተኛ መጠኑ 7 የሚሆኑ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ሲኖሩት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ደግሞ 6 የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ቀርበዋል፡፡ ነገር ግን በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች ሁለቱን የአደረጃጀት ስልቶች አመጣጥኖ በመጠቀም ረገድ ጉዱለት ታይቶባቸዋል፡፡
- ✓ በሁለቱም የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ከተደራጁት 21 የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ውስጥ 9ኙ ብቻ ተለጣጣቂነታቸው ሳይቆራረጡ ከደረጃ ደረጃ ወይም ከክፍል ክፍል ስፋትና ጥልቀት እንዱሁም ክብደት እየጨመሩ የሚሄዱ ሲሆኑ 21ዎቹ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ደግሞ ተለጣጣቂነታቸውን ያልጠበቁ ወይም የመቆራረጥ ችግር የሚታይባቸው መሆኑን መገንዘብ ተችላል፡፡
- ✓ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎችን የቃላት ቀትተኛ ና አገባባዊ ፍቺ የሚያሳዩ ዐ.ነገሮች መፃፍ፣ቃላት በዐ.ነገር ውስጥ እንደገና መፃፍ ግጥም መፃፍ ወዘተ የሚሉ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ተግባራት ለክሂሉ የተሰጠውን ትኩረት ያላመላከቱ መሆናቸውን በመማሪያ መጻሕፍቱ በተደረገው ፍተሻ ለማረጋገጥ ተችሎዋል፡፡
- ✓ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶችና ተግባራት በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ሲደራጁ ሙሉ በሙሉ የይዘት አደረጃጀት መስፈርትን ማለትም ተከታታይነት፣

ተለጣጣቂነት፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር መሰረት አድርገው ሙሉ በሙሉ በጥንቃቄ የተደራጁ ናቸው ለማለት አያስደፍሩም፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

በ9ኛእና በ10ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት በተመለከተ የተሰበሰቡ መረጃዎች ከተተነተኑና ከተብራሩ በኃላ በጥናቱ ውጤት መሰረት ከሚከተሉት መደምደሚያዎች ላይ ተደርሷል፡፡

- የ9ኛእና የ10ኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ምን ምን አይነት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች እንደተካተቱ በመለየት ተተንትነዋል፡፡
- በሰነድ ፍተሻና በቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት የተካተቱትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት በተለያዩ ደረጃ መሆኑንና ተከታታይነት፣ ተለጣጣቂነት፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የይዘት አደረጃጀት ተያያዥነት ያላቸው በጣም ጥቂት ቁጥር የሆኑ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል፡፡
- በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች የአደረጃጀት ስልቶች አመጣጥኖ በመጠቀም ረገድ ጉድለት ታይቶባቸዋል፡፡

## 5.3 የመፍትሔ ሀሳብ

አጥኚው ከላይ ከቀረበው ጥናት ማጠቃላያ ሀሳብ መሰረት በማድረግ የሚከተለትን የመፍትሄ ሃሳቦች አቅርቧል፡፡ በዚህ ጥናት ተተኳሪ ከሆኑት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ላይ የታዩ ጠንካራ ጎኖች የበለጠ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ የዚህ ጥናት አቅራቢ አስተያየት ነው፡፡ መማሪያ መጻሕፍት እንደገና ሲደራጁም ሆነ ሲሻሻሉ በጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ላይ የታዩ ድክመቶች እርምት ወይም ማስተካከያ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡ አጥኚው የሚከተሉትን የመፍትሔ ሀሳቦች አቅርቧል ፡፡

- ✓ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች የይዘት አደረጃጀት መርህ /መስፈርትን ተከትለው በእኩል ደረጃ እንዲደራጁ ማድረግ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ እንደሚያስችል እሙን ነው፡፡

- ✓ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚቀርቡ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በሁሉም የእርከኑ መጻሕፍት ውስጥ ተለጣጣቂነት/ ቀጣይነት/ እንዲኖራቸው ለማድረግ ትኩረት ሰጥቶ መስራት፤
- ✓ እንዳ አስፈላጊነቱ የተማሪዎች ዳራ መሰረት በማድረግ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስልት አደረጃጀት አመጣጥኖ ማቅረብ ወደ አንድ ስልት ብቻ አለማመዘን፤
- ✓ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የሚደራጁ ይዘቶች በአንድ የክፍል ደረጃ ላይ ብቻ ቀርበው በሌሎቹ ክፍሎች ስፋትና ጥልቀት ባለው ሁኔታ መቅረብ ካልቻሉ የሚያመጡት ለውጥ ዘላቂ አይሆንም፡፡ በጥናቱ በተጠቀሱት መጻሕፍት ውስጥም አንዳንድ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች በተወሰኑ ክፍሎች ብቻ ተጠቅሰው በሌሎች ሲዘለሉ ታይተዋል፡፡ ስለዚህ በሁሉም ተተኳሪ ክፍሎች ተከታትለውና ተለጣጥቀው ቢቀርቡ፣
- ✓ መማሪያ መጻሕፍት አንዴ ከተዘጋጁ በኃላ ዝግጅቱ አበቃለት ማለት አይቻልም፡፡ ተከታታይ የሆነ ግምገማ እየተደረገባቸው በየጊዜው እንዲስተካከሉ ማድረግ ያስፈልጋል ፡፡በዚህም መሰረት በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘት አደረጃጀት በተለያዩ የትምህርት ባለሙያዎች፣ መምህራንና ተማሪዎች ወዘተ እንዲገመግሙ እድል የመስጠት ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣
- ✓ የመጽሕፍ አዘጋጆች ከመርሀ ትምህርት አዘጋጆች ጋር ተወያይተው መማሪያ መጻሕፍት ሲያዘጋጁ እርስ በርስ ተናቦ የተሻለ መጽሕፍ ማዘጋጀትና ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡ በአጠቃላይ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ረገድ የተሻለ ውጤት ለማምጣት ሌሎቹን የቋንቋውን ክሂሎች ጨምሮ ተገቢ ትኩረት ቢሰጥ ይህም ከክፍለ ጊዜ ስርጭት አንጻር ፍተሻ ቢደረግበት፣ የሁለም ክሂሎች የይዘት ስርጭት ሚዛናዊ በሚሆን መልኩ ቢቃኝ ተማሪዎቹ የጽሕፈት ክሂላቸውን የሚያሻሽሉበት ዕድል ይኖራቸዋል፡፡ በዚሁ መልኩ የሚመለከታቸው የትምህርት አካላት በሙሉ ለጉዳዩ ትኩረት ሊሰጡ እና በዚህ መንገድ የተማሪዎችን ጽህፈት የሚዳብርበት ሁኔታ ሊያመቻቹ ይገባል፡፡

# ዋቢ መጻሕፍት

**ሰይድ ይመር**፡፡(1993)፡፡ “በዘጠነኛ ክፍል  የአማርኛ ቋንቋ መማሪያመጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን  የመጻፍ ክሂል ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ግምገማ፡፡” አዱስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ የቀረበ ጥናት(ያልታተመ)

**ተስፋዬ ሸዋዬ**፡፡(1981)፡፡ “ስነ-ልሳንና ቋንቋን ማስተማር፡፡ ”አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ  ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍል፡፡አዲስ አበባ፡፡(ያልታተመ)

**ተስፋዬ በቀለ**፡፡(1993)፡፡ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ለ8ኛ ክፍል አማርኛ አፊፊት ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ መፃሐፍ ውስጥ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ግምገማ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት፤ ለአማርኛ ማስተማር ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)

**ተሻለ ክፍሌ**፡፡(2005)፡፡ “በ2004አ.ም  በተዘጋጀው የዘጠነኛክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት፡፡”አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣አማርኛ ለማስተርስ ዲግሪ  ተዘጋጅቶ የቀረበ ጥናት ፡፡(ያልታተመ)

**አለም እሸቱ** ፡፡(1995)፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ የመማሪያና ማስተማሪያ ዝግጅት ውስጥ የክሂሎች አደረጃጀትና ትኩረት የሚሹጉዳዮች አወቃቀር፡፡ስ/ት/ጥ/ም /ኢንስቲትዩት፡፡

**አተነህ አወቀ** ፡፡ 1974፡፡ ‹‹‹የስነ-ጽሁፍ ትምህርት ይዘት በሁለተኛ ደረጃ/9-12/ የአማርኛ ቋንቋ ሥርኣተ ትምህርት ከ1966ዓ.ም. ወዲህ፡፡›› ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሁፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

**አያሌው አስፋው**፡፡ 1986፡፡ ‹‹ከ1933-1983ዓ.ም ባሉት አታት ውስጥ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪ መሕፍት ዝርዝር አይነትና የይዘት ግምገማ፡፡›› ለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ና ስነ-ጽሁፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

**ጌታቸው አዱኛ**፡፡ 1985፡፡ ለአረኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች የብቃት ደረጃ፡፡›› ለአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች

ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ ትምህርት ለማስተርስ ድግሪ ማሚያ የቀረበ ጥናት።

**ጥላሁን ገብረክርስቶስ።** (1990)።“ የአራተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ይዘትና ትንተና በተለይ ትግርኛ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎች የተዘጋጀ።”ለማስተር ማሚያነት የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)

**ፅጌታፌስ።** (1992)። “ለፅህፈት ክሂል የተመረጡ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እንዴት ተደራጅተዋል፣ በአዲስ አበባ መስተዳደር ትምህርት ቢሮ ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (5ኛ-8ኛ) ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ መጽሐፍ ላይ የተካሄደ የይዘት ትንተና ግምገማ።” አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ አማርኛ ለማስተርስ ዲግሪ ተዘጋጅቶ የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)

ያለው እንዳወቀ። (2001)። የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር። አዲስ አበባ፣ ንግድማተሚያቤት።

ByrneDonn(1991).TeachingWritingSkill.London:LongmanGroup.UK,L.Cunnings

CresWell, J.W (2009). Educational, Research, Planing, Conducting and Evluating quantitative and qualitative research.(3thed). Pearson Education, INC.

Cunningsworth.A.(1984). Evaaluating and selecting EFL Teaching Materials (5thprint).oxford:heine mann.

M.C Donough,J and C, Show .(2003).Materials and methods in ELT.Second edition oxford; Blackwell.

Grant,N(1987) .Making the most of Your text Book .london long man.

Hutchlson J.and Torres ,E.(1994)The text book as aent of change . Hong bong .Long man group LTd.

Harmer,J (1992)Teaching and Learning Grammar .London: Long man

worth,Alan.(1995).ChoosingYourCourseBook.London:Heinemanm.Hedge.T.(199

1).Writing.Oxford:OxfordUniversitypress.

Larsen Freeman D.(1991).Teachinig Gremmer.InCelce Murcia ,M. (ed) .TeachingEnglishas a second or Foreign Langauge .pp ,(279-295) .Boston ; HeinlPublisherse.

Nunan,D.(1988).SyllabusDesignOxford:Oxforeduniversitypress.

_________(1989).Dsinging Lernerss and theirCommunicativeClassroom. CambridgeCambridgeUniversitypress.

Nuttal,C.(1983).Teaching reading skills in foreign language.London; long man.

Raimes,A.(1983).TeachniquesinTeachingWriting.Oxford.oxfrdUniversty.

_________(1991).Out of thewoods:EmergingTradiions intheTeachingofWriting .TESOLQuarterly2513:407-430.

Richards,J.C.(2001).CurriculumDevelopmentinLanguagTeaching.CambridgeCambridge Universitypress.

Reachards and Rodjier (1986) Approches and method in Language Teaching .

Sheldon,G.(1987).ELT.TextbookAndMaterialsProbleminEvaluationAndDevelopmet.London.OPU.

Taba.Hilde.(1962).CurriculumDevelopment:TheorAndPractice.New YourkHarcourtofBrAceJovanovichInc.

Tyler.R.W.(1949). Basic principles of Curriculum and instruction .chicago: the univrsity of chicago press .

Ur.Penny.(1996). A Course inLanguage Teaching Practice and Theory Cambridge: Cambridge University Press.

Waod,E.(1995). Intrduction Grammar,Penguin:Penguin Group

Wallace,T.andet.Al.(2004). Teaching Speaking,Listing and Writing Belgiug,Brusels.International. Bureaofeducation(IBE)

Yeden,Janice(1987). Principles of CourseDesign for Language Teaching Cambridge: Cambridge University Press

# አባሪዎች

## ሀ. ከመጻሕፍት አዘጋጆች ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

ከዘጠነኛ ክፍል መጻህፍት አዘጋጆች ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

**ጥያቄ 1፡-** እርሶ ባዘጋጁት መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የመፃፍ ክሂልን የሚመለከቱ ይዘቶች ምን ምን ናቸው?

**መልስ፡-** እኛ ባዘጋጀ ነው የ9ኛ ክፍል መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የጽሕፈት ክሂል ይዘቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡ አቀራረባቸው ሥርዓተ ትምህርቱን መሰረት ያደረገ ሲሆን ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ አስር በቅደም ተከተል በተለያዩ ትዕዛዛት ታጅበው የቀረቡ ናቸው፡፡

ክፍት ቦታዎችን በቃላት መሙላት፣ ገላጭ ድርሰት መፃፍ፣ የኣባባሎች ምንነንነት በጽሑፍ መግለጽ፣አንቀጽ መጻፍ፣ ዘገባ መጻፍ፣ ገላጭ ድርሰት፣ አባባሎችን መግለጽ፣ የቃላትን ልዩነት በፅሁፍ ማብራራት፣ሥርዓተ ነጥብን በተገቢ ቦታ ማስገባት፣ ድርሰት መጻፍ፣አባባሎችን መግለጽ፣አረፍተ ነገሮችን በማስተካከል አንቀጽ መጻፍ፣የዘይቤ ምንነት እና አይነቶችን በጽሁፍ መግለጽ፣የደብዳቤ አፃፃፍ ሥርኣትን ተከትሎ ደብዳቤ መጻፍ ፣የታዋቂ ሰዎችን ታሪክ መጻፍ ወዘተ የሚባሉት የመጻፍ ክሂል ይዘቶች ናቸው፡፡

**ጥያቄ** 2፡-እርሶ ባዘጋጁት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂሌ ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት የይዘት አደረጃጀት መስፈርቶች ወይም መርሆች ይዘው ተገኛተዋል?

**መልስ** ፡- አዎ፤ የመፃፍ ክሂል ትምህርት አደረጃጀትን መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡ ሆኖም ይህ አንተ ራስህ በመገምገም ምላሽ የምትሰጥበት ሀሳብ ነው፡፡ የጥናትህ ዋና ዓላማም እነዚህን ጉዳዮች መመርመር ይመስለኛል፡፡ ማንኛውም መጽሐፍ ሲዘጋጅ መርሆዎችን መሰረት አድርጎ የሚዘጋጅ እንደመሆኑ ይህ መጽሐፍም መርሃ ትምህርቱን መሰረት በማድረግየተዘጋጀነው፡፡

**ጥያቄ 3፡-** እርሶ ባዘጋጁት የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ከአደረጃጀት መስፈርቶች አንፃር እንዴት ተደራጅተዋል?

**መልስ-** ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርሁት እነዚህን ጉዳዮች አንተ መጽሐፉን በመገምገም ምላሽ የምትሰጥባቸው ናቸው፡፡ እኛ እንደ አዘጋጅ መልሳችን ‹‹አዎ›› ነው፡፡ ምክንያቱም መርሃ ትምህርቱን መሰረት በማድረግ ያዘጋጀነው ስለሆነ፡፡ በተጨማሪም ከቀላል ወደ ከባድ፤ ከተራ ወደ ውስብስብ እየሰፋና እያደገ እንዲሄድ ለማድረግ ሞክረናል፤ ይህን ለማድረግም በቀረበው መርሃ ትምህርት ላይ ማስተካከያዎችን ለማድረግ ሞክረናል፡፡

ሀ . ከተከታታይነት አንፃር

..............................አዎ.....................................

ለ. ከተለጣጣቂነት አንፃር

......................................*አዎ*..........................................................

*ሐ. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አደረጃጀት አንፃር*

..................................................*አዎ*.....................................................

*መ. ከአጠቃ ላይ ወደ ዝርዝር አደረጃጀት አንፃር*

.............................................*?????አዎ*.........................................

**ጥያቄ** 4፡- በእርሶ ባዘጋጁት የዘጠነኛ ክፍል መፃሐፍ ከጽህፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት አንፃር እንከን የለሽ ነው ብለው ያምናሉ ?

**መልስ-** በመጀመሪያ ‹‹እንከን የለሽ›› በሚለው ሀረግ አልስማማም፡፡ ነገር ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ የተዘጋጀ መጽሐፍ እንደመሆኑ ድክመቶች ሊኖሩበት ይችላል፡፡

**ጥያቄ** 5፡-ይዘቶቹ የምርጫ መስፈርቶችን መሰረት አድርገዋል ብለው ያምናሉ?

**መልስ-** በመምረጫ መስፈርቶች መሰረት የተመረጡ ይመስሉኛል ለማንኛውም መሠረት ያደረግነው መርሐ ትምሕርቱን ነው፡፡

**ጥያቄ** 6፡-በመማሪያ መፅሐፉ ውስጥ የሚገኙት የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ተጨማሪ አስተያየተ ካሎዎት?

**መልስ-** ከአንቀጽእና ገላጭ ድርሰት አልፈን ሌሎች የድርሰት አይነቶችን እንዲለማመዱ ለማድረግ በመርሃ ትምህርቱ የተገደብን በመሆኑአልቻልንም፡፡

# ማረጋገጫ

በአማርኛ ቋንቋመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት የጽሕፈ ክሂል ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ንጽጽራዊ ግምገማ በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ማህበራዊ ሳይንስና ስነሰብዕ ኮሌጅ የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ሥነ -ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል በተግባራዊ ስነልሳን አማርኛን ለማስተ  ማስተርስ ለኤም. ኤ ድግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢዎች የተደረጉና አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማየን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም……………………………………………

ፊርማ…………………………………......

ቀን………………………………………………